ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 254 ግንቦት 14 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
– 0111 26 26 27 – 0922 11 53 24/26
– 0111 26 26 28 – 0922 72 74 48/49
– 0111 26 26 29 – 0922 72 38 70
– 0111 26 26 30 – 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

# ‹‹መከላከያ ሰራዊት ኢትዮጵያን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ ዝግጁነት ላይ ይገኛል››

- ዐቢይ አህመድ (ዶክተር)
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ

## • ኮሌጁ በደህንነት ስትራቴጂ ያሰለጠናቸውን ከፍተኛ ወታደራዊና ሲቪል አመራሮች አስመረቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የመከላከያ ሰራዊት በየጊዜው ራሱን እያዘመነ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ ዝግጁነት ላይ እንደሚገኝ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዐቢይ አህመድ (ዶክተር) ገለጹ።

የኢፌዴሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ በከፍተኛ ደህንነት ስትራቴጂ ያሰለጠናቸውን ከፍተኛ ወታደራዊና ሲቪል አመራሮች አስመርቋል።

ዶክተር ዐቢይ ኮሌጁ ለመጀመሪያ ጊዜ በደህንነት ስትራቴጂ ያሰለጠናቸውን 38 ከፍተኛ ወታደራዊና ሲቪል አመራሮችን ትናንት ባስመረቀበት ወቅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት ገደማ መከላከያ አገር ለማስቀጠል ሳይሆን ሕልውናውን ለማስቀጠል ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞት ነበር።

ተግዳሮቱ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስም ራሱን ለማደራጀት መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል። የገጠመው ፈተና መከላከያ ራሱን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ በሚያስችል መልኩ ለማደራጀትና አስተማማኝ ተቋም ለመገንባት ትልቅ ዕድል ነው።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት የመጀመሪያና ዋና ተልዕኮው ኢትዮጵያን ማስቀጠል ነው። ኢትዮጵያ በታሪኳና በሕዝብ ብዛቷ ታላቅ አገር በመሆኗ መከላከያ በታሪኳ ልክ ዘመኑን በሚመጠን መንገድ ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በመታጠቅ ራሱን ማደራጀት ይጠበቅበታል።

ራስን ሰውቶ ኢትዮጵያን ለማስቀጠል የሚያስችል ብቃት ለመላበስ መሰልጠን አስፈላጊ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶክተር)፤ አብዛኛው የዲፕሎማሲ፣ ስትራቴጂ፣ የአመራር ጥበብና በቴክኖሎጂው ዘርፍ የተገኘው እውቀት ከመከላከያ በመሆኑ ተመራቂዎች ብዙ ማንበብ፣ ማወቅና በቁርጠኝነት መስራት እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

የማይሞት ታሪክ ለመስራት መማር፣ ታሪክን እና

‹‹መከላከያ ሰራዊት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያዘጋጀው "ስለኢትዮጵያ" የተሰኘ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ በድሬዳዋ ከተማ ተከፈተ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ድሬዳዋ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያዘጋጀው "ስለኢትዮጵያ" የተሰኘ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ በድሬዳዋ ከተማ በይፋ ተከፍቷል።

81 ዓመቱን ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሚያከብረው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዕለቱ በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይትም አዘጋጅቷል።

"ስለኢትዮጵያ" የተሰኘውን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴና የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ትናንት በድሬዳዋ ከተማ በይፋ መርቀው ከፍተዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል ከፎቶ አውደ ርዕዩ መከፈት በኋላ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ያዘጋጀው "ስለኢትዮጵያ" የተሰኘው የፎቶግራፍ አውደርዕይ በአይነቱ ሳቢና የታሪክ ዑነቶችን በሚስብ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡ ዳኘ አበራ

# "የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን በዘላቂነት ለመፍታት የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ይገባል"

- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስቴር

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ድሬዳዋ፡- በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ የሚያጋጥመውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በዘላቂነት ለመፍታት የአገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ ሁሉም ጥረት ማድረግ አለበት ሲሉ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትሮች አስታወቁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በድሬዳዋ ከተማ ያዘጋጃቸው "ስለኢትዮጵያ" የተሰኘው በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮረው የፓናል ውይይት ትናንትና ተካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል የዘርፉን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ጽሁፍ ሲያቀርቡ እንደገለጹት፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግርን ለመፍታት የመጀመሪያውና መሠረታዊው መፍትሄ የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ነው።

አሁን የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም 50 በመቶ ነው፤ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረው የማምረት አቅም ማነስ በሚፈለገው ደረጃ ምርት እንዳይቀርብ አድርጓል። በቀጣይ የአምራቹን አቅም ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ውጥን ተይዟል ብለዋል።

አምራች ዘርፉ ከአጠቃላይ የአገሪቱ ጂዲፒ የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ እንዳለው የጠቆሙት አቶ መላኩ፤ ድርሻውን ወደ 17

"የውጭ ምንዛሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ከገበያ ውጪ ሆነው የቆዩ ከ 118 በላይ ኢንዱስትሪዎች ወደ ማምረት ተመለሱ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በአገር ደረጃ በመናበብና በቅንጅት እየተሰራ በመሆኑ ከማምረትና ከገበያ ውጪ ሆነው የቆዩ ከ118 በላይ የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንደተመለሱ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ዳይሬክተር ወይዘሮ አበባ ታመነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት ፣ በኢትዮጵያ ከማምረትና ከገበያ ውጪ ሆነው የቆዩ ከ118 በላይ ኢንዱስትሪዎች ወደ ማምረት መመለስ ችለዋል።

በአገራችን «ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ 118 በላይ የሚሆኑ የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች እንዴት መከፈትና ሥራ መጀመር አለባቸው? በቀጣይም በተለያዩ ምክንያቶች ሊዘጉ ከጫፍ የደረሱት ደግሞ እንዳይዘጉና ከገበያ እንዳይወጡ ማድረግ አለብን በሚል ሰፊ የንቅናቄ ሥራ ተጀምሮ እየተሰራ ነው።

ሥራውን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን ከአጋር አካላቶችና ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ኢንዱስትሪዎቹን የማምረት አቅማቸውን እንዴት መጨመርና ማሳደግ ይቻላል፣ ኢንዱስትሪዎቹ ያላቸውን የማምረት አቅምስ እንዴት መጠቀም ይችላሉ? ያሉባቸውን ችግሮች እንዴት እንፍታ? ምርትና ምርታማነትን እንዴት ከፍ እናደርገ? ዘርፉን እንዴት ከፍ እናደርግ? የሚል አላማ ያለው ንቅናቄ እየተካሄደ ነው



ወይዘሮ አበባ ታመነ

ብለዋል።

ወይዘሮ አበባ በገለፃቸው ፣ ዘርፉ የተለያዩ ማነቆዎች ያሉበት ነው። የዘርፉን ማነቆዎች በትብብርና በቅንጅት በጋራ ሆኖ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ንቅናቄው ይፋ ከተደረገ ወዲህ የተለያዩ ለውጦች በኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ መጥተዋል ያሉት ወይዘሮ አበባ፣ ዘርፉን ለማልማት በአጋርነትና በትብብር ተቀናጅቶ መስራት ያስፈልጋልም ብለዋል።

በኢትዮጵያ የተወሰኑ ንቅናቄው ያልተደረገባቸው ክልሎች መኖራቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ አበባ፣ ንቅናቄው ባልተደረገባቸው ክልሎችም በቅርቡ ይደረግባቸዋል ብለዋል።

ተዘግተው የነበሩ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ ችግሮች እንዳሉባቸው የተናገሩት ወይዘሮ አበባ፣ ዋና ዋናዎቹ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ በየአካባቢዎች በተፈጠሩት የፀጥታ ችግር፣ በመሰረተ ልማት እጥረት፣ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ እና የተለያዩ የምርት በግብዓት ችግር ምክንያት እንደሆነ አመልክተዋል።

በንቅናቄ ስምምነቱም የክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎችም በመሰረተ ልማት ችግር ላይና ከመሬት አቅርቦት ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆኑን ወይዘሮ አበባ አውስተው፣ ከማምረትና ከገበያ ውጪ የሆኑ ፋብሪካዎችን ወደ ሥራ ለመመለስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

የመስሪያ ገንዘብ እጥረት የገጠማቸውን ፋብሪካዎችን ችግር ለመቅረፍም ከተለያዩ የገንዘብ ድርጅቶችና አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

አንድም ፋብሪካ በገንዘብ እጥረት፤መሰረተ ልማት እጦትና በሰላም መጓደል ምክንያት ሊዘጋ አይገባም ያሉት ወይዘሮ አበባ ሲዘጋ በሥሩ ያለውን ሰራተኛና ቤተሰቦቹ ላይ ችግር እንደሚፈጠርና በሂደትም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ጫና ከፍተኛ እንደሆነ አብራርተዋል።

ኢንዱስትሪውን ማበልጸግ ስንችል መዋቅራዊ ሽግግሩን ማፋጠን እንችላለን። በዚህም ምርት ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ የመመለሱ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላልም ብለዋል።



## የወጣቶችን ስብዕና ለመገንባት ሁሉም ኃላፊነቱን እንዲወጣ ተጠየቀ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች ስብዕናቸው እንዲገነባ ከቤተሰብ ጀምሮ፤ ትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሚዲያ እና ሁሉም ማህበረሰብ በየደረጃው ኃላፊነታቸውን ሊወጡና አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚገባ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አዘጋጅነት በከተማው 11ዱም ክፍለከተሞች ለሁለት ወራት " የወጣቶች ስብዕና ልማት ለአገራዊ ህብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ ሲካሄድ የቆየው ፌስቲቫል የማጠቃለያ መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡

በፌስቲቫሉ ወጣቶች በኪነጥበብ፣ በስፖርት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች አቅማቸውን እና ችሎታቸውን ሲያሳዩ መቆየታቸው በመርሐ ግብሩ ተገልጿል፡፡

በመዝጊያ ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሙና አህመድ እንደተናገሩት፤ ወጣቶች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው በአእምሮ የበለጸጉ እንዲሆኑ ሰፊ ሥራዎች በማዕከላት ሲሰሩ ቆይተዋል።

ወንድማማችነትን ከመገንባት አኳያ ተግባሩ እንደ ጅምር እንደሚበረታታ፣ ታዳጊዎች ላይ መስራት የተሻለ ሀገር ለመገንባት ወሳኝ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡ ሌሎች ክልሎችም ተሞክሮ በመቀመር የወጣቶች የስብዕና ግንባታ ሥራዎችን ማጠናከር አለባቸው ነው ወይዘሮ ሙናያሉት ።

እንደ አገር ከሶስት ሺህ በላይ የስብዕና ግንባታ ማዕከላት ቢኖሩም በትክክል አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት አንድ ሺህ 545 ማዕከላት ናቸው፡፡ ወጣቶች የሀገር ተረካቢዎች ብቻ ሳይሆኑ ባለቤቶችም በመሆናቸው በወጣቶች የስብዕና ግንባታ አደረጃጀት እና አሰራሩን በማስተካከል የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውንም ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብርሃም ታደሰ በበኩላቸው፤ ወጣቶች ላይ መስራት መጪውን ጊዜ ብሩህ ማድረግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የስብዕና ግንባታው በሁሉም ዘርፍ ተጠናክሮ መቀጠል ስላለበት ቢሮው ኃላፊነት ወስዶ እየሰራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

በሁሉም ክፍለ ከተሞች ከ700 በሚበልጡ ክበባት ከ16 ሺህ በላይ ወጣቶች በኪነጥበብ ዘርፍ እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ፣ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ወጣቶችም በስብዕና ግንባታው ተሳትፎ ማድረጋቸውንና በከተማው የሚገኝ አጠቃላይ ወጣት አንጻር የበለጠ መስራት እንደሚያስፈልግ አቶ አብርሃም ተናግረዋል፡፡

በስብዕና ግንባታው የተሳተፉ ወጣቶችም መርሐ ግብሩ ያላቸውን ችሎታ እንዲወጡ እንዳገዛቸው እና ልምድ በመቅሰም መልካም ስብዕና እንዲላበሱ እንደረዳቸው ተናግረዋል።

በመድረኩ በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ፣የአዲስ አበባ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና ከ11ዱም ክፍለከተሞች የተውጣጡ ወጣቶች ተሳትፈዋል።

በመዝጊያ መርሐ ግብሩ በወጣት ሰዓሊያን የተሳሉ ስዕሎች እና የፈጠራ ሥራዎች ለዕይታ የቀረቡ ሲሆን በወጣቶቹ የተዘጋጁ የሙዚቃ እና ዳንስ ትርዒቶች ቀርበዋል። የደም ልገሳም ተደርጓል።




## ኮርፖሬሽኑ ከአንድ ሺህ በላይ መጽሐፍ ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍ ድጋፍ አደረገ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ትኩረታቸውን በኢንጂነሪንግና በሳይንስ ዘርፍ ያደረጉ ከአንድ ሺህ በላይ መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍ ድጋፍ ማድረጉን የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አዲሱ ማሞ ትናንት በተከናወነው የርክክብ መርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ ኮርፖሬሽኑ ማሕበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ለአንድ ወር ያክል ሲያካሂድ በቆየው በማሰባሰብ ያገኛቸውን ለትውልድ ይጠቅማሉ ያላቸውን መጽሐፍት አስረክቧል።

ለቤተ መጽሐፉ የተበረከቱት መጽሐፎች በኢንጂነሪንግና በሳይንስ ዘርፍ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው። መጽሔቶችን ለማሰባሰብ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያሉ ባለሀብቶችን ማህበራዊ ኃፊነታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል የማስተባበር ሥራ ተሰርቷል ብለዋል አቶ አዲሱ።

በቀጣይነት የመጽሐፍ ማሰባሰብ ተግባሩ እንደሚቀጥል በመጠቆም፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ባለሀብቶችን በመቀስቀስ ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍ ትናንት ከተሰበሰበው በላይ መጽሐፍትን ለማሰባሰብ እንደሚሰራም ቃል ገብተዋል።

በተለይ የውጭ ባለሀብቶችን በመጠቀም ከሀገር ውጭ የሚገኙ መጽሐፍቶችን ለቤተ መጽሐፉ ለማሰባሰብ እንደሚሰሩም ተናግረዋል።

በኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበው ወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል ነው። አሁን የሚሰበሰቡ መጽሐፍቶች ወደፊት ወጣቱን በመቅረጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉና የኢንዱስትሪ ልማቱን በዘላቂ መሰረት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እንደሚያግዙ አስረድተዋል።

የአብርሆት ቤተ መጽሐፍት ዳይሬክተር አቶ መስፍን ገዛኸኝ በመጽሐፍት ርክክቡ ወቅት እንደገለጹት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የተሰማሩ የውጭ ባለሀብቶች በመጽሐፍ ማሰባሰቡ ላይ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ

እንዲሰበስቡ መጋበዛቸው ትልቅ ተስፋ መሆኑን በመጥቀስ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

መጽሐፍት መስጠት ከሁሉም በላይ ስጦታ ነው። አብርሆት ቤተ መጽሐፍት እንደ ቤተ መጽሐፍት የንባብ አገልግሎትን መስጠትና የንባብ አገልግሎትን ለቱሪዝም መጠቀምን መሰረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

በተያያዘ ዜናም የግራዝማች ኢንተርቴይመንት ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብሩክ ግርማ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍ በርካታ መጽሐፍትን ለማሰባሰብ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑንም አስታውቀዋል።

መጽሐፍት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በመሆኑ ሁሉም የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በአንድ ቀን 20 ሺህ መጽሐፍትን ለማሰባሰብ ሰኔ አምስት ቀን ከ8 ሰዓት ጀምሮ በአብርሆት ቤተ መጽሐፍ ግቢ ታላቅ የሙዚቃና የኪነ ጥበብ ዝግጅት ይካሄዳል የመግቢያ ዋጋ ሁለት መጽሐፍት ይዞ መገኘት መሆኑንም አቶ ብሩክ ጠቁመዋል።

በዕለቱ በቦታው መገኘት የማይችሉ ግለሰቦች ቀደም ብለው መጽሐፍ ማስረከብ እንደሚችሉም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሕገ መንግስታዊነት ወደ ብልጽግናው ማማ፣ ወደ ሰላሙ ከፍታ መውጣት ይገባል !

"ሕግ" የግዜር፣ የሰው ደንብ፣ ውሳኔ፣ አታድርግ የሚል፣ ሥርዓት፣... ተጽፎ ታትሞ የሚወጣ፣ የሚታወጅ፣ የሚነገር፣... »የሚል ትርጉምን ይይዛል። ከዚህ አኳያ ሕግ ማለት ሰዎች በማህበራዊ ግንኙነታቸው፣ በኢኮኖሚያዊ ጉድኝታቸው፣ በፖለቲካዊ መስተጋብራቸው የሚኖራቸውን እንቅስቃሴ የሚወስኑበት፤ መልካምና መልካም ያልሆኑ ተግባሮቻቸውን ለይተው የሚገሩበትና የሚያርሙበት፣... የአድርግ አታድርግ ሥርዓታቸውን የሚወስኑበት የጋራ ስምምነት ሰነዳቸው ነው ማለት ያስችላል።

ይሄ ወደ አገር ሲያድግ ደግሞ የአንድ አገር ዜጎች በአንድነት፣ በፍቅር፣ በመተባበርና በሰላም አብሮ ለመኖራቸው እንደ መመሪያ ሆኖ ግንኙነታቸውን በመልካም ግንኙነት የተቃኘ የሚያደርጉበት፤ ከዚህ መርህ ያፈነገጠውን በሕግ ሰነዳቸው ታግዘው ወደ መስመር የሚመልሱበትና ሰላምና አንድነታቸውን ለማጽናት የሚጠቀሙበት ነው።

ሕዝብና ሕግ ካላቸው የአንዱ አንዱን የመጠበቅና የማረም ጉድኝት ባሻገር የሁለቱ ጥምረት የላቀ ውጤታማ እንዲሆን ሕግን የሚያስፈጽም አካል የግድ ሊኖር ይገባል። ይህ አካል ደግሞ መንግስት ነው፤ መንግስት በዜጎች ይሁንታ የተቀረጸ ዜጎችን የሚዳኝበት የመንግስት ሕግ (ሕገ መንግስት) ያስፈልገዋል። ሕገ መንግስቱም የአንድ ሉዓላዊት አገር መንግስት አገርን በመምራት ሂደት፣ ሕዝብን በማስተዳደር ተግባሩ ሊፈጽመው እና ሊያስፈጽምው ግድ የሚለውና በመሃላ የተቀበለው የጋራ ቃልኪዳን ሰነድ ነው። ከዚህ አንጻር ሕግ እና ሕገ መንግስት ሰዎች በተለያየ መንገድ ካኖሩት መስመር ሲያልፉ ሊታረሙበትና ሊገዙበት በጋራ ይሁንታቸው የቀረጹት ሰነድ ሲሆን፤ ለዚህ ሰነድ የመገዛት እና ከሕግ በታች ሆኖ የመኖር ባህላቸው ደግሞ ሕገመንግስታዊነታቸውን የሚረጋገጡበት ተግባራቸው ነው።

በዚህ መልኩ መንግስት ሕግን ለማስከበር ሲሰራ፤ ሕዝብም ለሕግ የመገዛትና በሕግ የመመራት ባህሉን ሲያሳድግ፣ ግዴታውን ሲወጣ፣ አገር ሰላም ትሆናለች፤ ሕዝቦች በሰላማዊ ግንኙነታቸው በጋራ ለአገር ሁለንተናዊ ብልጽግና ይተጋሉ። ይሄን ያደረጉ አገራት፤ በሕግ ተመርተው፣ ለህግ ተገዝተውና ሕገ መንግስታዊነትን ተላብሰው የሚኖሩ ዜጎች ያሉባቸው ናቸው። ከሕግ የሚያፈነግጡ ግለሰቦችና ቡድኖች ሲያጋጥሙ ደግሞ በሕግ ወደመስመር የሚመልስ፤ ገፋ ሲልም ቀጥቶ አደብ የሚያስይዝ መንግስት የፈጠሩ አገራትም ይሄንን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን አድርገው፤ የተሟላ ሰላማቸውን ማረጋገጥ ችለዋል።

በኢትዮጵያም ይሄን እውን የማድረግ ጽኑ ፍላጎት ያለ ቢሆንም፤ የታሪኳን፣ የጥበብ ገጿን፣ ያልተቆራረጠ የመንግስት ሥርዓቷንና መሰል የገናንነቷን ቁመና የሚመጥን ሕገ መንግስታዊነትን ማስፈን ሳይቻል አገር በየወቅቱ በሚስተዋሉ ለሕግ ያለመገዛት አዝማሚያዎች ስትረበሽ፣ በኢኮኖሚዋም፣ በሰብዓዊ ሃብቷም የከፋ ጉዳት እየደረሰባት ቆይታለች።

ይህ ሕገመንግስታዊነትን ያለመላበስ አካሄድ የዜጎች ወይም የመንግስት አካላት ተብሎ መወሸቂያ የሚሰጠው የተናጥል ችግር ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። ይልቁንም ዜጋው እንደ ዜጋ፤ መንግስትም እንደ መንግስት ሕግን አክብሮ ከመንቀሳቀስ እንዲሁም ሕግ የሚከበርባትን አገር ከመፍጠር እና ይህ እውን እንዲሆን ሕግን በማስከበር ረገድ እየተሰራ ያለውን ስራ በወጉ ፈትሾ ሁሉም ራሱን እንዲመለከት የሚያሳስብ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ሃቅ ነው።

ይህ ሲባል፣ ሕዝብ እንደ ህዝብ ይገዛኛል ብሎ ላዘጋጀው የሕግ ሰነድ ራሱን ከማስገዛትና ሌሎች ሕግን ተላልፈው የሚገኙ ኃይሎች ሲኖሩ ተው ብሎ በሕግ ስም ከመገሰጽ አኳያ ያለበትን ደረጃ ሊፈትሽ ይገባዋል። በዚህም በሕግ የተሰጡ መብትና ግዴታዎችን፣ ፈቃድና ክልከላዎችን በአግባቡ ተገንዝቦ በተቀመጠው አግባብ መጓዝ አለመጓዙን መለየት ይኖርበታል።

ከዚህ ባለፈም ሕግ ጥሰው የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሲኖሩ ሌላ የሕግ አስከባሪ አካል ሳይጠበቅ እኔም ሕግ አስከባሪና የሕግ ጠበቃ ነኝ ብሎ ካልተገባ ተግባራቸው እንዲታቀቡ ከማድረግ አኳያ ያለውን ሰብዕናና ሃላፊነት መመርመር ይጠበቅበታል።

መንግስትም እንደ መንግስት የሚመራው ሕዝብ የሕግ ግንዛቤ እንዲኖረው ከማድረግ ጀምሮ በሕግ የመምራት፣ ሕግ የሚተላለፉትንም የመገሰጽና የመቅጣት ልምምዱን ማጤን ይኖርበታል። ሕዝብ እንደ ሕዝብ፣ መንግስትም እንደ መንግስት በመካከላቸው ሥርዓት ሆኖ እንደ ድልድይ ግንኙነታቸውን የሚወስነውን ሕግና ሕገ መንግስታዊነትን መላበስ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ከዚህ ረገድ ራሳቸውን መፈተሽ እና ሕግ አውቆ የማሳወቅ፤ ሕግ ጠብቆ የማስጠበቅ፤ ሕግ አክብሮ የማስከበር ሰብዕናን የተላበሰ መንግስትና ሕዝብ እንዲኖር በማድረግ የሚፈለገውን አገራዊ ሰላም፣ አንድነትና ብልጽግና ማምጣት ይጠበቃል።

ይህ ግን በኢትዮጵያ ትናንትም ሆነ ዛሬ በሚፈለገው ልክ አልተገለጠም። ለዚህም ነው ዛሬ በየቦታው ሥርዓት አልበኞች እየተፈለፈሉ ወደ አሸባሪነት ሲሸጋገሩ የሚታዩት። ለዚህም ነው ዜጎች በግፈኞች እየተገፉና በግፍ እየተገደሉ የሰላምና ደህንነት ስጋት አልፋታቸው ያለው። ለዚህም ነው ዛሬ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመስራት መብታቸው አጣብቂኝ ውስጥ የገባው። ለዚህም ነው እዚህም እዚያም ሥርዓት አልበኞች ባሻቸው ተጓዥ ሆነው ለመታየት ብቻ ሳይሆን ፍላጎታቸውን በተግባር ለመግለጥ ሲፍጨረጨሩ የሚታዩት።

እነዚህ ሁሉ ከሕገመንግስታዊነት ያፈነገጡ እኩይ ተግባራት በሕግ አሰራር ሊገቱ የግድ ነው፤ ሕዝብ እንደ ህዝብ ለህግ መገዛትና ሌሎችም ከእኩይ ተግባራቸው እንዲታረሙ መትጋት፤ መንግስትም እንደ መንግስት ለሕግ የበላይነት መከበር መንግስታዊ ኃላፊነቱንም፣ በትሩንም ሊጠቀም የተገባ ነው። ይህ ሲሆን ነው ሕገ መንግስታዊነት ሊሰፍን፤ ሰላምና ደህንነታችንም ሊረጋገጥ፣ በሕገ መንግስታዊነት ወደ ብልጽግናው ማማ፣ ወደ ሰላሙ ከፍታ መውጣት የሚቻለው።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## "ነፃነትንና መብትን ከለላ በማድረግ የሚፈፀም የትኛውም አይነት እኩይ ተግባርን መንግስት አይታገስም!"

*- የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፤*

የዜጎች ሰላም፣ ደህንነትና የአገር ቀጣይነት የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ሲከበር ብቻ እንደመሆኑ፤ ነፃነትንና መብትን ከለላ በማድረግ የሚፈፀም የትኛውም አይነት እኩይ ተግባርን መንግስት አይታገስም ሲል የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ የጸጥና እና የሕግ ማስከበር ተግባራት ላይ በማተኮር ከትናንት በስቲያ ባወጣው መግለጫ አስገንዝቧል።

አገልግሎቱ በመግለጫው እንዳመለከተው፤ የዜጎች ሰላም፣ ደህንነትና የአገር ቀጣይነት የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ሲከበር ብቻ ነው። በመላ ኢትዮጵያ የሚገኘው ዜጋ በሰላም ወጥቶ የመግባት መብቱ እንዲከበርና ደህንነቱ እንዲጠበቅ የህግ የበላይነትን ማስፈን ደግሞ ህዝብ ለመንግስት የሰጠው ኃላፊነት ነው። የዜጎች ነፃነትና ዲሞክራሲም መስፈን የሚችለው የትኛውም ጉልበት አለኝ የሚል አካል ከህግ በታች መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ብቻ ነው። በመሆኑም ነፃነትንና መብትን ከለላ በማድረግ የሚፈፀም የትኛውም አይነት እኩይ ተግባርን መንግስት አይታገስም።

የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ከትናንት በስቲያ ያወጣውን ሙሉ መግለጫ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤

**የዜጎችን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም የአገርን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ብቸኛው መፍትሄ የህግ የበላይነትን ማስከበር ነው!**

በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚታየውን ህገወጥነትና የሰላም መደፍረስ እንዲሁም ስርዓት አልበኝነትን መንግስት እንዲቆጣጠር መላ ህዝባችን በተደጋጋሚ በአንድ ድምፅ ሊባል በሚችል መልኩ ሲጠይቅ ቆይቷል። ቀደም ሲል ብሔራዊ የፀጥታ ም/ቤት እነዚህን ጉዳዮች በመገምገም አስፈላጊው እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ማስታወቁም የሚታወስ ነው። ከሰሞኑ አዲስ አበባን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች ውስጥ የፌደራልና የክልል የፀጥታ ኃይሎች እየወሰዱት ያለው ህግ የማስከበር እርምጃ የዚሁ አካል ነው።

በኦሮሚያና በአጎራባች ክልሎች የሸኔ የሽብር ቡድን ከሌሎች የጥፋት ኃይሎች ጋር በመተባበር ህዝባችን ላይ እያደረሰ የነበረውን ጥቃት ለመቀልበስ መንግስት የተሳካ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል። በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች በአልሸባብ የሽብር ኃይል ላይ እየተወሰደ የሚገኘውም እርምጃ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ከሰሞኑ ደግሞ በአማራ ክልል በህገወጥ የጦር መሳሪያና ገንዘብ ዝውውር፤ በቡድን ተደራጅቶ ግለሰቦች ያፈሩትን ሃብትና ንብረት በመዝረፍና በማውደም ላይ የተሰማሩ፤ በነፍስ ግድያ የሚጠረጠሩ፣ አንዱን ህዝብ ከሌላው ጋር በማጋጨት ክልሉ እንዳይረጋጋ በሚያደርጉ ቡድኖች ላይ መጠነ ሰፊ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል። በአዲስ አበባና በዙሪያው ኦሮሚያ ከተሞች በቡድን ተደራጅተው በልዩ ልዩ የዝርፊያ ወንጀሎች ላይ የተሰማሩ፣ የጦር መሳሪያና የገንዘብ ዝውውር አቀባባይ በሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች፤ እንዲሁም በወያኔ ሰርጎ ገቦች ላይም መንግስት ቁርጠኛ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል። በሁሉም ክልሎች እየተካሄደ በሚገኘው ኦፕሬሽን በርካታ ግለሰቦችና ቡድኖች ከነ ትጥቆቻቸው፤ ከዘረፉት ንብረትና ቀጣይ ሊፈፅሙ ያቀዷቸዉ ጥፋቶችን ካሰፈሩባቸው ሰነዶች ጋር በቁጥጥር ስር እንዲውሉ እየተደረገ ነው። ጉዳያቸውም ተገቢውን ሂደት ጠብቆ እየተጣራ ለፍርድ እንዲቀርቡ እየተደረገ ይገኛል።

መንግስት ህግና ስርዓትን በማስከበር የዜጎች ደህንነትና የአገር ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እየወሰደ ላለው እርምጃ መላው ህብረተሰብ ከፍተኛ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል። በሁሉም ክልሎች መላው ህዝባችን የጥፋት ሰንሰለቶቹን ከማጋለጥ ጀምሮ አጀንዳውን የሁከትና ብጥብጥ ማስፈፀሚያ ለማድረግ የሚጥሩ ኃይሎችን እየታገለ ይገኛል። በአንፃሩ የተለያዩ ስያሜዎችን በመስጠት የመንግስትን እርምጃ ለማጠልሸት የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች መኖራቸውን መንግስት አረጋግጧል። አሸባሪው ሕወሓት እና ጀሌዎቹ መንግስት እየወሰደ ባለው እርምጃ ሁከትና ብጥብጥ ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ህገወጥ ቡድኖችን በተለይም በአማራ ክልል የህግ የማስከበር ስራዎችን ለማደናቀፍ የሚሞከሩ ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን ለማባባስ ከወዲሁ አጋርነታቸውን በይፋ እየገለፁ ነው። ይህ የሚያመለክተን እነዚህ ቡድኖች በተለይም በፋኖ ስም የሚነግዱ የዝርፊያ ቡድኖች በህዝባችን ላይ ከፍተኛ ክህደት የፈፀሙ ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች እና የተላላኪዎቻቸው ዓላማ ማስፈፀሚያ መሆናቸው ነው።

መላው ህዝባችን ይህንን እኩይ ሴራ በመገንዘብ መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ በመደገፍ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ መንግስት ይጠይቃል። ለሃሰተኛ መረጃዎችና የጥፋት መልእክትን ለያዙ ወሬዎች ጆሮ ባለመስጠት የህግ የበላይነትን የማስከበሩን እርምጃ እንደ እስካሁኑ በሙሉ አቅሙ ማገዙን እንዲቀጥልም ጥሪውን ያቀርባል። መንግስት በበኩሉ በህገወጥ ተግባር ላይ በመሳተፍ፤ ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ሆን ብለው፤ አቅደው በሚሰሩ አካላትና ግለሰቦች እንዲሁም የሚዲያና የጋዜጠኝነት ካባ ደርበው ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ የሚወሰደውን የማያዳግም እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል።

የዜጎች ሰላም፣ ደህንነትና የአገር ቀጣይነት የሚረጋገጠው የህግ የበላይነት ሲከበር ብቻ ነው። በመላ ኢትዮጵያ የሚገኘው ዜጋ በሰላም ወጥቶ የመግባት መብቱ እንዲከበርና ደህንነቱ እንዲጠበቅ የህግ የበላይነትን ማስፈን ደግሞ ህዝብ ለመንግስት የሰጠው ኃላፊነት ነው። የዜጎች ነፃነትና ዲሞክራሲም መስፈን የሚችለው የትኛውም ጉልበት አለኝ የሚል አካል ከህግ በታች መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ብቻ ነው። ነፃነትንና መብትን ከለላ በማድረግ የሚፈፀም የትኛውም አይነት እኩይ ተግባርን መንግስት አይታገስም። መንግስት በሆደ ሰፊነት በተደጋጋሚ ጊዜ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ከቁብ ያልቆጠሩ ኃይሎችን መግታት የሚቻለው የህግ የበላይትን በማስከበር ብቻ ነው። ሁሉም ዜጋና የተለየ አመለካከት ያላቸው ወገኖችም መብትና ጥቅሞቻቸውን ማስከበር የሚችሉት የህግ የበላይነት ሲረጋገጥና ሰላም ሲሰፍን ብቻ ነው።

**የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት!!**

**ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

ዜና

# <<ልጆቻችን ሰላማዊ አገር እንዲረከቡ የምንፈልግ ከሆነ ለአገራዊ ምክክሩ ትኩረት መስጠት አለበት>>

*- ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ*


**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ልጆቻችን ሰላማዊ አገር እንዲረከቡ የምንፈልግ ከሆነ ለአገራዊ ምክክሩ ሁሉም በየዘርፉ የድርሻውን እና የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት ሲሉ ሽማግሌው ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ተናገሩ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ልጆቻችን ሰላማዊ አገር እንዲረከቡ የምንፈልግ ከሆነ ለአገራዊ ምክክሩ ሁሉም በየዘርፉ የድርሻውን እና የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት።

እንደዚህ አይነት ትልቅ እድል ሁልጊዜ የማይገኝ እንደሆነ ገልጸው የመጨረሻም ባይሆን ከመጨረሻዎቹ አንዱ በመሆኑ ሁሉም ለዚህ አገራዊ ምክክር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰሩ አነጋገር በአገራዊ ምክክሩ



የማንስማማባቸው አንኳር የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በችግሮቹ ላይ በመወያየት በሚደረስባቸው ውሳኔዎች በአጭር እና በረጅም ጊዜ የሚለወጡ ነገሮች እንደሚኖሩ ጠቁመው በአገራችን እየተስተዋለ ያለውን የእልህ ፖለቲካ እንዴት ማስተካከል እና መግራት አለብን የሚለው ትልቁ ጥያቄያችን መሆን አለበት ብለዋል፡፡

የማህበረሰቡ መዋደድ እና እርስ በእርስ መፈቃቀር በተወሰነ መልኩ እየተጎዳ በመሆኑ ቅራኔ የሚፈጥሩ ነገሮችንም ለይቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በአገራዊ ምክክሩ የሃይማኖቶች አብሮ የመኖር እና እርስ በእርስ ያለመከባበር ችግር እየተስተዋለ የመጣበትን ምክንያቶችን ለይቶ መፍትሄ ማበጀት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው በምክክሩ ኢትዮጵያ ለሁሉም የምትበቃ አገር መሆኑዋን በመተማመን የማህበረሰቡን መዋደድ እና እርስ በእርስ መፈቃቀር ወደ ነበረበት እንዲመለስ ማገዝ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡

ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ እንደገለጹት፣ ለችግሮች መፍትሄ ሲበጅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ የየአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ እና ችግር ለይቶ ማወቅ እና በዛ መሰረት መፍትሄ መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ሁሉም የየራሱን ድርሻ ከተወጣ እና ከተባበረ ችግሩን መፍታት ይቻላል፡፡

በአገራዊ ምክክሩ ሶስት ነገሮች እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ ተናግረው ችግሩን ማወቅ እና መለየት ፣ለችግሩ የመፍትሄ አቅጣጫ ማመላከት እና ሂደቱን በስርዓቱ ለመገንዘብ መሞከር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

አገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን እልህ መግታት የሚቻልበት ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ነገሮችን የምናፈርሰው በእልህ ነው ያሉት ፕሮፌሰሩ እልህ መግታት ከቻልን ችግራችንን መረዳት እና መፍትሄ ማምጣት እንችላለን ብለዋል፡፡ ለቀጣይ ትውልዶች ሰላማዊ እና ከድህነት የተላቀቀች ኢትዮጵያን ለማስረከብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለአገራዊ ምክክሩ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

## <<መከላከያ ሰራዊት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አገር ማስቀጠልን ማወቅ ይጠይቃል።

መከላከያ እውቀትን አብዝቶ በመፈለግ ያገኘውን እውቀት በማካፈል መጓዝ ይገባዋል። የማይጨበጥ ነበልባል ለመሆን መማር ይጠይቃል። በእውቀታችሁ፣ በድካማችሁ አንድ በመሆን ኢትዮጵያን ማስቀጠል እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

መከላከያ የመልካም የአስተዳደር፣ የፖሊሲና የስትራቴጂ እውቀቶች የሚገኙበት ተቋም ነው። መማር ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር ማድረግና እውቀትን አብዝቶ በመፈለግ ዘመኑ የደረሰበትን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ራስን ማብቃትና ማዘመን አስፈላጊ መሆኑንም ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኮሌጁ ዋና አላማ ብቁ አመራሮችን የመፍጠርና በደህንነትና የጸጥታ ተቋማት የሚታየውን የአመራር ክፍተት በመሙላት እየተወሳሰቡ የመጡ አገራዊ ፈተናዎችን በብቃት መመከት ነው።

የመከላከያ ሰራዊት ግዳጆችን በድል አድራጊነት የመፈጸም አቅሙ ማደጉን በመጠቀም፤ ተመራቂዎች አገራዊ አስተሳሰብ በመያዝ በቅንጅት መስራት እንደሚጠበቅባቸውም አመልክተዋል።

የኮሌጁ አዛዥ ብርጋዴር ጀኔራል ቡልቲ ታደሰ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፋዊና አካባቢያዊ የደህንነት ስጋት በኢትዮጵያ የሰላምና ደህንነት ላይ የሚያሳርፈውን ጫና በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቋቋም የከፍተኛ ደህንነት ስትራቴጂ አመራር ስልጠና አስፈላጊ ነው።

የአገርን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ በተለይም በአሸባሪነት፣ በዓለም አቀፍ ወንጀል፣ በህገ ወጥ የጦር መሳሪያና የሰው ዝውውር እንቅስቃሴዎችን መግታት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ በትኩረት መስራት እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል።

ተመራቂ አመራሮቹ ሰላም ለማስፈንና የአገርን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ተግባር ቁልፍ ሚና ለመጫወት የሚያስችል ነው ብለዋል።

## የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መልኩ የቀረበበት ነው።

የፎቶግራፍ አውደ ርዕዩም ከ1950ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ የነበረውን የፖለቲካ ውጣ ውረድ፣ የህዝብ እንቅስቃሴና የአገር ሁኔታዎችን የሚያሳይ ነው። ፤ በአውደ ርዕዩ ላይ የቀረቡ ፎቶግራፎችም ከንጉሱ ዘመን ጀምረው ያሉ የታሪክ ሁነቶችን የሚያሳዩና በአጭር ደቂቃ በርካታ መጽሐፍ አንብቦ የመጨረስ ያክል ጠቃሚና ገላጭ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ብለዋል።

ይህ የፎቶግራፍ አውደርዕይ ለድሬዳዋ ከተማ ህዝብ ክፍት መሆኑና ለሚጎበኙ ሰዎች እንደትልቅ ዕድልና አጋጣሚ ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለታሪክ ምስክር የሆነውን አውደርዕይ በማቅረቡ ምስጋና ይገባዋል ብለዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ፤ አውደርዕዩ በታሪክ አጋጣሚ ያሉ ክስተቶችን የሚያሳይና ጠቃሚ ሃሳቦች የሚገኙበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የታሪክ ሁነቶችን በመሰነድ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ላይ አተኩሮ እየሰራ ይገኛል፤ ይህንን ጥረቱንም አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ይህን አይነት ሳቢ አውደርዕይና የኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት በማዘጋጀቱ ላመሰግን እወዳለሁ ብለዋል ሚኒስትሩ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ



አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው እንገለጹት፤ በአውደ ርዕዩ ከአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት በተለይም ደግሞ ከ1960ዎቹ አንስቶ የነበሩ መሪዎች ምን ራዕይ ነበራቸው? በየዘመናቱ የተነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ምን ምልክ ነበራቸው የሚለውን በዝርዝር ያሳያል።

በተጨማሪ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማትና የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ የነበሩ ወሳኝ ኩነቶችን የሚዳስስ የፎቶግራፍ አውደርዕይ ቀርቧል፤ አገራዊ ለውጡን በተመለከተ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ፈተና፣ ድልና ተስፋ የሚያመላክት ዝግጅት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

"ስለኢትዮጵያ" የተሰኘው የፎቶ ግራፍ አውደርዕይና የፓናል ውይይት በ11 የተለያዩ ክልል ከተሞች እንደሚካሄድ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የድሬዳዋው መርሐግብር ሁለተኛ ዙር መሆኑን ገልጸዋል።

በድሬዳዋ የተከፈተው የፎቶ አውደ ርዕይ ከግንቦት 13 ቀን ጀምሮ እስከ ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ለሕዝብ ክፍት ሆኖ እንደሚቆይ ታውቋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከ1960ዎቹ እስካሁን ያለውን የአገሪቱን ፖለቲካዊ ጉዞ የሚያመላክት የፎቶ መጽሐፍ አዘጋጅቶ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ማስመረቁ የሚታወስ ነው።

## "የውጭ ምንዛሪ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል፤ ይህም ምርታማነት ከማሳደግ ባለፈ የውጭ ምንዛሪ እጥረትንም ለማቃለል አይነተኛ መፍትሄ ይሆናል ብለዋል።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በቀጣይ ዓመታት በአገሪቷ ጂዲፒ ከ17 በመቶ በላይ ድርሻ እንዲኖረው እየተሰራ ነው፤ መንግሥት ዘርፉን ለማጠናከር በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአቅም ማጠናከር ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከመንግሥት ጥረት ባለፈ ባለሃብቱም ተገቢውን የኢንዱስትሪ አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ እንዳለበት ተናግረዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ መንግሥት በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ እየሰራ መሆኑን ገልጸው፤ ባለሀብቶች የሚያነሱትን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በቅድሚያ ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንደሚኖርባቸው አመልክተዋል።

የአገሪቷ የዕድገት ሞተር የሆነው የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በሀገር በቀል ኢኮኖሚው ዋነኛ ትኩረት እንደተሰጠው ያመለከቱት አቶ አህመድ፤ በመንግሥት በኩል መሠረተ ልማትን ማስፋት፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን ማሳደግና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ቢሮክራሲ ለማቅለል የሚረዱ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አመልክተዋል።

ዘርፉን ለማሳደግ ደግሞ ከመንግሥት ባሻገር በዋናነት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ያሉት አቶ አህመድ፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ምርታማነታቸውን በማሳደግ ኢኮኖሚው ላይ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ማጎልበት ይችላሉ ብለዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃላፊ አቶ ጀማል አህመድ በግሉ ዘርፍ ያለው የአምራች ኢንዱስትሪ ተግዳሮቶችና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ባቀረቡት ጽሁፍ እንደገለጹት፤ መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያደርገውን ድጋፍ ማሳደግ አለበት፡፡ በተለይ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን በፍትሐዊነት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ዘርፉን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

የአገር ውስጥ አምራቹ ከውጭ አገራት ግብይት ከሚያገኘው የንግድ ሥራ ያገኛትን የውጭ ምንዛሪ ለተጨማሪ ኢንቨስትመንት የማዋል ፍላጎት አለው፤ በመሆኑም ለውጭ አገር ባለሀብቶች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ለአገር ውስጥ ባለሃብቱም በመስጠት አምራቹን መደገፍ ይገባል ብለዋል።

በአምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ የሚያጋጥሙ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ መንግሥትም ከግሉ ዘርፍ ጋር ያለውን ትብብር እያጠናከረ ከሄደ በአምራቾች ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመቅረፍ ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል።

መንግሥት ለአምራች ኢንዱስትሪው በሰጠው ትኩረት በዘርፉ ለውጦች ተመዝግበዋል ያሉት አቶ ጀማል፤ ሚድሮክ ላይ በተደረገ ሪፎርምና አገራዊ ድጋፎች ከአምናው ገቢ አንጻር እጥፍ መገኘቱን አስታውቀዋል።

መንግሥትም ህዝቡም መወቀስ ካለበት በአገር ውስጥ ምርት መጠቀም ላይ ያለባቸው ከፍተኛ ውስንነት መሆኑን አንስተው፤ እንደ አገር የኢትዮጵያን ምርት የመጠቀም ንቅናቄ መፍጠርና መተግበር ከተቻለ ከፍተኛ እመርታ ማምጣት እንደሚቻልም ነው የተናገሩት፡፡

በፓናል ውይይቱ የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር የከተማዋን ኢንቨስትመንት አማራጮች የሚያሳይ ጽሁፍ አቅርበዋል። በመድረኩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳንዱካን ደበበ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እንዲሁም የተለያዩ የፌዴራልና የክልል አመራሮች ተገኝተዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## በኒውክሌርና በሳይበር የታገዘ 3ኛው የአለም ጦርነት መባቻ...!?

የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዎ ጉተሬዝ የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት በተጀመረበት ሰሞን በሰጡት መግለጫ የኒውክሌር ጦርነት ሊቀሰቀስ እንደሚችል፤ በዚህም መላው የሰው ልጅ ላይ አደጋ እንደተደቀነና በአስቸኳይ ጦርነቱ ቆሞ በሰላማዊ ድርድር እንዲቋጭ ጥሪ አድርገዋል። ቻይና፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ፈረንሳይ፣ ሕንድ፣ እስራኤል፣ ፓኪስታን፣ ራሽያ፣ ዩናይትድ ኪንግደምና አሜሪካ በአጠቃላይ 13 ሺህ 80 የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ታጥቀዋል ቢባልም፤ 90 በመቶው ማለትም 11 ሺህ የአሜሪካና የራሽያ ነው። ከዚህ ውስጥ ሁለቱ አገራት እኩል ድርሻ እንዳላቸው ይገለጻል። ይፋ ያልሆኑ መረጃዎች ግን በአለማችን የሚገኘውን የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ብዛትን እስከ 20 ሺህ ያደርሱታል።

### የሰሜን ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት

የሰሜን ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት /ኔቶ/ የተመሰረተበት መርህ የማዕዘን ድንጋይ በአንቀጽ 5 ላይ የተደነገገው ከአባል አገራቱ አንዱ ቢጠቃ በጋራ መከላከል/collective defence/የሚለው ነው። የሕብረቱ አባል የሆኑ 30 አገራት እንደተጠቁ ስለሚቆጠር በአንድነት የመሰለፍ ግዴታ አለባቸው። የቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት አካል የነበሩት እነ ላቲቪያ፣ ሉቲኒያና እስቶኒያ ዛሬ ሉዓላዊና የኔቶ አባል ስለሆኑ አንዳቸው በራሽያ ጥቃት ቢደርስባቸው በቀላሉ የ3ኛው የአለም ጦርነት ለዛውም በኒውክሌር የጦር መሳሪያና በሳይበር ታግዞ ሊቀሰቀስ ይችላል። ይህ ደግሞ የአለም መጨረሻ አርማጌዶን ሆነ ማለት ነው።

አንድ የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የማጥፋት አቅም ሲኖረው በአካባቢና ህይወት ባላቸው ሌሎች ፍጥረታት ላይ ዘላቂ ጠንቅ የማምጣት ጉልበት አለው። ለዚህ ነው አለም የራሽያን እና የዩክሬንን ጦርነት እያወገዘው ያለው። በነገራችን ላይ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነት ላይ የዋለው በ2ኛው የአለም ጦርነት ሲሆን፤ ጥቅም ላይ ያዋለችውም አሜሪካ ነች፡፡ በወቅቱም ጃፓንን ለማጥቃት ተጠቅማበታለች። በዚህም 2ኛውን የአለም ጦርነት መቋጨት ቢቻልም ወደ 226 ሺህ የሚጠጉ ባብዛኛው ሰላማዊ ሰዎችን በመፍጀት ዛሬ ድረስ ጠባሳው ሳይሽር አለ።

የCNN Global Public Square /GPS/አዘጋጅ ፋሪድ ዘካሪያ እና ሌሎችም እንደሚሉት፤ የራሺያ ዩክሬን ጦርነት የድህረ የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመንን ወደቀደመው ቆፈን የመለሰ ነው፡፡ ዳግማዊ ቀዝቃዛው ጦርነትም ተቀስቅሷል። የድህረ ቀዝቃዛው ዘመን 30 አመታት እያለፈባቸውና እየጨረሱ ነው። በእነዚህ አመታት ቻይና ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ኃያልነቷን አረጋግጣለች። ኢኮኖሚዋ በአለማችን በሀብት ደረጃቸው ከ3ኛ እስከ 6ኛ የሚገኙትን አገራት ድምር አክሏል። የራሽያ ተፅዕኖም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን በማስታወስ የአለም ሁኔታ እየተለዋወጠ መሆኑን ፋሪድ በማስረጃ ይሞግታል።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን፣ ራሽያውያንን የናዚ አቀንቃኝ ከሆነው የኪየቭ መንግስት ጭቆና ለመታደግ ያሉትን ልዩ ዘመቻ ሲያስጀምሩ፤ ውሳኔው ለሌሎች ያስተላለፈው መልዕክት የሚመስለኝ የኒውክሌር የጦር መሳሪያን በአንደኝነት የታጠቀች አገር ገዥ ስለሆነ የሁሉንም ትኩረት የሳቡ መሆናቸውን ነውር። እንደተሰጋው የንግግሩን ማሳረጊያም፤ "ጣልቃ ለመግባት የሚሞክር አገር ካለ፤ በታሪኩ አይቶትና ሰምቶት የማያውቅ የራሽያ መብረቃዊ የአጸፋ ምላሽ ይከተለዋል፤ " ካሉ በኋላ በመቀጠል፤ ኒውክሌርን እናንተም ብትታጠቁት የእኛ ግን ከእናንተው የላቀ ስለሆነ አርፋችሁ ተቀመጡ በማለት ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል፡፡

እንደተፈራውም መልዕክቱ አለምን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ብርክ አስያዘ። የሰው ልጅ ያለ ልዩነት በቃ ሲፈራ የኖረው የኒውክሌር ጦርነት መባቻ ላይ ተደረሰ ማለት ነው ብሎ እንዲጠይቅ ተገደደ። ሕዝበ አዳም የፕሬዚዳንት ፑቲንን ማስፈራሪያ በቅጡ አንስቶ ሳይጥል፤ ለማብሰልሰያ በቂ ጊዜ ሳያገኝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሰርጌ ላቭሮቭ ከቀናት በኋላ ብቅ ብለው፤ " 3ኛው የአለም ጦርነት የሚቀሰቀስ ከሆነ እንደቀደሙት ሁለት የአለም ጦርነቶች አይነት ሳይሆን የኒውክሌር ጦርነት ነው የሚሆነው፤ " ሲሉ የፑቲንን ማስፈራሪያ ደገሙት፤ አጸኑት።

ይህ የፕሬዚዳንት ፑቲን ማስጠንቀቂያ አለምን ከአጽናፊ እስከ አጽናፍ በድንጋጤ ክው ከማድረጉ ባሻገር ላልተጠበቀው አደጋ እንዲዘጋጅ ከጥልቅ የንጋት እንቅልፉ አባኖታል። የኒውክሌር ጦር መሳሪያ የታጠቁ አገራትም ሙከራ ባያደርጉም መዘጋጀታቸው አይቀርም። መጨረሻው ምን እንደሚሆን መገመት ቢያዳግትም አሜሪካ ይሄን በመፍራትና ራሽያን ላለመተንኮስ የአገር አቋራጭ ባልስቲክ ሚሳይሏን ሙከራ ለማራዘም፤ በዩክሬን ከበረራ ነጻ የአየር ክልል ለማስፈን እንደማትንቀሳቀስ ደጋግማ ቃሏን ሰጥታለች። ሁኔታዎች በዚህ ስለመቀጠል አለመቀጠላቸው እርግጠኛ መሆን ግን አይቻልም።

የታዋቂው የ"ፎሪን አፌርስ"መጽሔት ጸሐፊዎች ኤማ አሽፎርድና ጆሹዋ ሽፍሪንሰን በዚያ ሰሞን ባስነበቡን ማለፊያ መጣጥፍ፤ ራሽያ የአሜሪካንና የምዕራባውያንን ጫና መቋቋም ቢሳናትና ተስፋ በመቁረጥ የኔቶ አባል በሆነ አንድ አገር የሳይበር ጥቃት ብትፈጽም እንኳ በሌሎች አገራት ጭምር እንደተፈጸመ ስለሚቆጠር የአባል አገራቱን በቀላሉ ስቦ ወደ ጦርነቱ ሊያስገባ ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ያጋባሉ። ጦርነቱ ከተጀመረ ወዲህ የራሽያ አራት የጦር አውሮፕላኖች የስዊድንን የአየር ክልል ጥሰው ገብተው እንደነበር የሚናገሩ አሉ፤ በሰላም ጊዜ እንደዚህ ያሉ አጋጣሚዎች በመነጋገር ሊፈቱ ይችላሉ። እንደአሁኑ ባለ ቀውጢ ሰዓት ግን በተለይ የኔቶ አባል አገራትንም ሆነ የራሽያን የአየር ክልል መጣስ የተፈራውን ጦርነት ሊጠራ ይችላል። በነገራችን ላይ በገለልተኝነትና በአፍቃሪ ሰላምነት የሚታወቁት ስዊድንና ፊንላንድ የኔቶ አባል ለመሆን ማመልከቻ አስገብተዋል።

አሜሪካና ምዕራባውያን ዩክሬን አለንልሽ፤ ከጎንሽ ነን ሲሏት ከርመው ጦርነቱ ሲጀመር እና ከተሞቿ ወደ ፍርስራሽነት ሲቀየሩና ወደ ድንጋይ ዘመን ሲመለሱ ምንም ባለማድረጋቸው በምንተ እፍረት የጦር መሳሪያ እርዳታውን እያጎረፉት ነው። ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ደግሞ እርዳታው የሚገባው የኔቶ አባል በሆኑ የጎረቤት አገራት አማካኝነት ስለሆነና ራሽያም እየገጠማት ያለውን ጫና ለመቀልበስ የዩክሬን ተባባሪ በምትላቸው አገራት ላይ ጥቃት ከፍታ ጦርነቱን ልታሰፋው ትችላለች የሚለው ሌላው ስጋት ነው።

"ፎሪን አፌርስ" እስካሁን የሁሉም ኔቶ አባል አገራት እያሳዩት ያለው ሕብረት አስገራሚ ቢሆንም ዩክሬንን በጦር መሳሪያ መርዳትና ማስታጠቅ ላይ አጠንክረው እየወተወቱ ያሉት ግን የራሽያ ጎረቤቶች እነ ፖላንደ፣ እስቶኒያ፣ ላቲቪያና ሉቲኒያ መሆናቸው ለራሽያ ብቀላ ካጋለጣቸው፤ የኔቶ አባል አገር ስለሆኑ ወደ 3ኛው የአለም ጦርነት ሊወስዳቸው ይችላል ሲል ስጋቱን ያጋራል። ሌላው ራሽያ ዩክሬንን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረችና መንግስት ከለወጠች ጦርነቱ ጎረቤት አገራትን መሰረት ወዳደረገ የሽምቅ ውጊያ ስለሚቀየር፤ በእነዚህ አገራት የሚገኙ የዩክሬን የአማጽያኑን ማሰልጠኛና ወታደራዊ ካምፖችን ካጠቃች ኔቶን ጎትቶ ወደ ጦርነቱ ያስገባል ይላል- "ፎሪን አፌርስ"።

የኔቶና የራሽያ ግጭት ተባብሶ በኒውክሌር የታገዘ ጦርነት ሊያስከትል ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት መፍጠሩ እንዳለ ሆኖ የታሪክ ልሒቃን ግን ኒውክሌር አልባ 3ኛው የአለም ጦርነት ሊቀሰቀስ ይችላል እያሉ ነው። ራሽያና ቻይና በ1960ዎቹ፤ ሕንድና ፓኪስታን በ1999 ዓ.ም ካርጊሊ ላይ የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ታጥቀው እያለ ነገር ግን ጥቅም ላይ ሳያውሉ ተዋግተዋል በማለት ታሪክን በዋቢነት ይጠቅሳሉ። (በነገራችን ላይ ሁሉም የዘመን አቆጣጠሮች እንደ አውሮፓውያን ናቸው፤)

ይሁንና ጦርነቱ ሊሰፋና አለማቀፍ ሊሆን የሚችለው ሁሉም የጦርነቱ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተሳታፊዎች ከፍ ብሎ ለማሳየት የተሞከሩ ስጋቶችን በጥበብና በማስተዋል ለማለፍ ከመሞከር ይልቅ አንዳቸው የተሳሳተ ውሳኔ ካሳለፉ ነው። የራሽያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ዩክሬንን የመውረር ውሳኔ አልያም የአውሮፓ ሕብረትንና ኔቶን የመቀላቀል የዩክሬን ውሳኔ ስህተት ይሁን አይሁን አከራካሪ ቢሆንም፤ የማናቸው ውሳኔ ስህተት እንደነበር ወደፊት ታሪክና ትውልድ ያልተዛባ ፍርድ ይሰጣል። የ3ኛው የአለም ጦርነት ለዛውም በኒውክሌር የጦር መሳሪያና በሳይበር ታግዞ ሊቀሰቀስ 11ኛው ሰዓት ላይ መገኘቱ ግን እርግጥ የሆነ ይመስላል።

ጦርነቱ በእርግጥ ከተቀሰቀሰ ደግሞ የአለም መጨረሻ፣ ምጽዓት ወይም አርማጌዶን ሆነ ማለት ነው። ለዚህ ነው የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ የራሽያና የዩክሬን ጦርነት የሁለቱ አገራት ወይም የራሽያና የምዕራባውያን የውክልና/proxy/ጦርነት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆች ጦርነት ነው ያሉት። ለዚህ ነው ጦርነቱን ሁሉም በጥፍሩ ቆሞ በአንክሮ የሚከታተለው። ኢኮኖሚያዊ ዳፋው ከወዲሁ በነዳጁ፣ በብረቱ፣ በስንዴውና በዘይቱ አገራችንን ጨምሮ በአለም ላይ ተገልጧል። ራሽያ ኔቶ እንደ ክፉ ድንበርተኛ በምስራቅ በኩል ሲገፉ ሲገፉ እንደ አምባዬና ምሽጌ የማያትን ዩክሬንን በመጠቅለል የህልውናዬና የደህንነቴ ስጋት እየሆነብኝ፤ በዩክሬን ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዜሌኒስኪ የሚመራው መንግስትም የአውሮፓ ሕብረት አባል በመሆን ለእኩይ አላማው አብሮ እያደመብኝ ነው በሚል በስጋት የተጀመረው ጦርነት 4ኛ ወሩን ይዟል።

የጦርነት ታሪክ አጥኚ ልሒቃን ገና ከአሁኑ ከ2ኛው የአለም ጦርነት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓ የተከሰተ ጦርነት ብለውታል። ጦርነቱንም የ2014 ዓም ተከታይ አድርገው ይወስዱታል። ዩክሬናውያን የክብር አብዮት ብለው ባቀጣጠሉት የጎዳና ላይ ነውጥ የአገሪቱን ከአውሮፓ ሕብረት መቀላቀል የሚቃወሙትንና ለሞስኮ ያደሩትን ፕሬዚዳንት ከስልጣን ያባርራሉ። መፈንቅለ መንግስት በምትለው በዚህ ለውጥ የተበሳጨችው ራሽያ በ2014 ዓ.ም የወደብ ከተማ የሆነችውን ክሬሚያን ጦር አዝምታ ጠቀለለች። በራሽያ የሚደገፉ ተገንጣይ አማጽያን ደግሞ የዩክሬንን ደቡባዊ ምስራቅ አካል የሆነችውን ዶንባስ ተቆጣጠሩ።

በ2021 ደግሞ ራሽያ ጦሯን ወደ ዩክሬን ድንበር በስፋት አስጠጋች። በዚህ የተነሳም ቀጣናዊ ውጥረት ነገሰ። ቭላድሚር ፑቲን ደግሞ የዩክሬንን ሉዓላዊ አገርነት ጥያቄ ውስጥ በማስገባት በዘወርዋራ የራሽያ አካል ናት አሉ። ኔቶም የራሽያ የደህንነት ስጋት መሆኑን ገለጹ። በአናቱ ዩክሬን አውሮፓ ሕብረትን እንደማትቀላቀል መተማመኛ እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ምዕራባውያንም ሆኑ ዩክሬን ሉዓላዊ አገር ስለሆነች ሕብረቱን የመቀላቀል የማይገሰስ መብት እንዳለት ቆፍጠን ብለው ገለጹ።

ፑቲንም ዩክሬን የራሽያኛ ተናጋሪዎች ላይ ዘር ማጥፋት እየፈጸመች መሆኑን በመግለጽ ክስ አቀረቡ፤ የኒውክሌርና የባዮሎጅካል የጦር መሳሪያ ባለቤት ልትሆን ስለመሆኑም ተናገሩ፤ ዩክሬንም ይሄን ክስ አስተባበለች፡፡ አሜሪካና ኔቶም የዩክሬን ሀሳብ ተጋሩ። ራሽያም እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ ኸረ በፍጹም እያለች ስታስተባብል ቆየች፡፡ በመጨረሻም የካቲት 21 ቀን 2022 ዓም በራሽያ የሚደገፉ አማጽያን በኃይል ለተቆጣጠሯቸው የዶኔስክና ሉሀንስክ ሪፐብሊኮች እውቅና ሰጠች። በበነጋው የራሽያ ፌደሬሽን ምክር ቤት ጦሩ እነዚህን አካባቢዎች እንዲቆጣጠር በሙሉ ድምጽ ወሰነ። የካቲት 24 ቀን 2022 ዓም የዩክሬንን ጦር ለማሽመድመድና ከናዚ ለማጽዳት ወታደራዊ ዘመቻ መጀመሩን ፑቲን ይፋ አደረጉ።

የተቀሰቀሰውን ጦርነት ተከትሎም በሚሳይልና በአየር ድብደባ የታገዘ ጥቃት ተከፈተ። እግረኛው የራሽያ ጦርም በተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ዩክሬን ገሰገሰ። ይሄን ተከትሎ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮልዲሚየር ዜለንስኪ የአስቸኳይ ጊዜና ክተት አወጀ። ራሽያ ከቤላሩስና ከዶንባስ አቅጣጫ ከባድ ወታደራዊ ጥቃት ከፈተች። ሆኖም ዩክሬናውያን ያልጠበቀችው የመከላከልና መልሶ የማጥቃት ውጊያ ገጥሟትም ነበር።

ከዚህም ባለፈ በፑቲን ላይ ከዋሽንግተን እስከ ብራስልስ፤ ከቶሮንቶ እስከ ፓሪስ፤ ከለንደን እስከ ሲውዲን የውግዘት ውርጅብኝ ተዥጎደጎደ። ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያና ሲንጋፖር ሳትቀር ፑቲንን አይንህን ለአፈር አሉት። የምዕራባውያን ቀኝ እጅ የሆነው የመንግስታቱ ድርጅት ኢኤስ_11/1 የተባለ ውሳኔ አሳለፈ። አሜሪካና ምዕራባውያን ተናበውና ተቀናጅተው የሞስኮው የሸርክና ገበያ ላይ ኢኮኖሚ ማዕቀብ ጣሉ። የራሽያው መገበያያ ሩብል ተጽዕኖ ላይ ወድቆ የነበረ ቢሆንም አሁን ማንሰራራት መጀመሩ እየተዘገበ ነው። ከ300 በላይ ኩባንያዎች ከሞስኮ ወጡ።

ራሽያም 51 የምዕራባውያን ኩባንያዎች ላይ አጸፋዊ ማዕቀብ ጣለች። በተደጋጋሚ ከምዕራባውያኑ የሚጣል ማዕቀብና ጫና ትንኮሳን ሊያስከትል በማሰብ በፕሬዚዳንቷ አማካኝነት የካቲት 27 ቀን 2022 ዓ.ም የኒውክሌር ጦሩ በተጠንቀቅ እንዲቆምና እንዲጠባበቅ ትዕዛዝ ሰጠች፡፡ በዚህም አለም በእውኑም ሆነ በሕልሙ ያላሰበው የኒውክሌር ጦርነት ደጁ ላይ ቆሞ እያንኳኳ መሆኑን ተረዳ። አውሮፓ ከ1990ዎቹ የዩጎዝላቪያ ቀውስ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በዩክሬናውያን ተፈናቃዮች እየተጥለቀለቀች ነው። እስካሁን ወደ 6 ሚሊየን የሚጠጉ ዩክሬናውያን ከአገር ውጭ፤ ወደ 8ሚሊየን የሚጠጉ ደግሞ በአገር ውስጥ ተፈናቅለዋል። ጦርነቱ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ የተፈናቃዮች ቁጥር በእጅጉ ሊያሻቅብ ይችላል ተብሎ ተሰግቷል። በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ወታደሮችና ሰላማዊ ሰዎች ሞተዋል።

ታዋቂው የታሪክ ሊቅ ፓል ኬኔዲ "The Rise and Fall of the Great Powers," በሚለው መጽሐፉ፤ አገራት ባልተፈለገ ጦርነት ዘው ብለው እየገቡ ራሳቸውን ለበረታ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየዳረጉ እድሜያቸውን ያሳጥራሉ ሲል ይገልጻል። አሁንም እየሆነ ያለው ይሄ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በጦርነቱ ራሽያ ዩክሬንን ልታንበረክክ ትችላለች። በሒደቱ ግን እሷም ከመጎዳት አትድንም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ ከኒውክሌር ጦርነት ስጋት ነጻ የሆነ አለም ለሁሉም ታስፈልጋለች!

ቸር ይግጠመን፤ አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## "በየትኛውም የጋዜጠኝነትም ሆነ የፎቶ ሪፖርተርነት ታሪክ ውስጥ እንደእኔ አገሩን ጦር ሜዳ ሄዶ ያገለገለ የለም፤ ስድስት ጊዜ ጦር ሜዳ መሄዴ በጣም ያኮራኛል"

*- አቶ ክንፈሚካኤል ሀብተማርያም*
*አንጋፋ የፎቶግራፍ ባለሙያ*

አፀገነት አክሊሉ

**የተወለዱት በ 1948 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ አፍንጮ በር በሚባል አካባቢ ነው። ከአራት እህትና ወንድሞቻቸው መካከል ለቤተሰባቸው ሁለተኛ ልጅ የሆኑት አቶ ክንፈሚካኤል ሀብተማርያም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ውስጥ ለረጅም ዓመታት የፎቶግራፍ ባለሙያ በመሆን ያገለገሉ፤ በዚህ የስራ ቆይታቸው ደግሞ አብዛኛቹን የጦር ግንባር ውሎዎች በካሜራቸው ያስቀሩ ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በርካታ የዓለም አገራትን የዞሩ በጠቅላላው ስራና ህይወት ብዙ ያስተማራቸው፤ ለሌላውም አርዓያ መሆን የሚችሉ አንጋፋ ባለሙያ ናቸው። እኛም ዛሬ ከህይወት ገጽታ አምዳችን ላይ የእኝህን ሰው ታሪክ ልናካፍል ወደናል።**



አቶ ክንፈሚካኤል ሀብተማርያም እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በቀጥታ ያመሩት ወደ ቄስ ትምህርት ነበር። በዛም ለአምስት ያህል ጊዜያት ዳዊትን በመድገም ነው ወደ መደበኛ ትምህርት የገቡት። መደበኛ ትምህርታቸውን በአመሃ ደስታ ትምህርት ቤት "ሀ " ብለው የጀመሩ ሲሆን ቀጥሎም ጉስቋም ኋላም ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ችለዋል። በወቅቱ የመንግስት ለውጥ ማለትም የአፄ ሀይለስላሴ መንግስት ወድቆ ደርግ መንበረ ስልጣኑን የተቆናጠጠበት ጊዜ ነበርና የፖለቲካውን ትርምስ ለማምለጥ ብሎም ተምሮ እራስን ለመቻል በማሰብ ወደ ኢትዮጵያ ፈጣን ሙያ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ገቡ። በሙያ ማሰልጠኛውም በኮንስትራክሽን መስክ ላይ ፕላን ማንበብ። ኤሌክትሪክ ስራና የእንጨት ሙያን ሰለጠኑ። መመረቂያቸው በደረሰ ጊዜ ግን ሌላ የህይወት አጋጣሚ ጠራቸውና ወደ ኮንስትራክሽን ሙያው ሳይመለሱ ቀሩ።

እዚህ ላይ ይላሉ " የኮንስትራክሽን ትምህርቴን እየተማርኩ ጎን ለጎን ፎቶ ቤት የከፈተ ጓደኛዬ ጋር እውል ነበር። በወቅቱም የፎቶግራፍ አነሳስ። ካሜራ አያያዝን አይ ነበር፤ እየቆየሁ ግን ለሙያው ከፍተኛ ፍቅር እያደረብኝ መጣ "።

ፎቶ ቤት መዋል ከፍተኛ የሆነ የፎቶግራፍ ፍቅር በውስጣቸው እንዲኖር ያደረጋቸው አቶ ክንፈሚካኤል በወቅቱ ፎቶ እንዴት እንደሚነሳ። እንዴት ተደርጎ ታጥቦ ለባለቤቱ እንደሚመለስ እንዲሁም ሰርጎች በሚበዙበት ወቅትም እራሳቸውን ችለው ሰርተው እንዲመጡ እድል ይሰጣቸው ጀመር፤ ይህ ደግሞ ሙያውን ለማዳበር ከፍተኛ እድል ፈጠረላቸው።

ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ፎቶ ቤት ተቀጥረው ስራን ለመስራት ያሰቡት፤ እንዳሰቡም አልቀሩም ስራውን ጀመሩ፤ ነገር ግን ፎቶ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ከእለት ፍጆታ ባለፈ ህይወትን ከፍ የሚያደርግ ገቢ ሊገኝበት እንደማይችል ተረዱ። በወቅቱም ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ችግርም አጋጥሟቸው ስለነበር ፊታቸውን ወደሌላ የስራ መስክ ማዞርን መረጡ። የገንዘብ ችግራቸውንም ለማለፍ በተማሩበት የኮንስትራክሽን ስራ ለመግፋት ፈለጉና ጀመሩት፤ ነገር ግን ያም አልነበረምና የእሳቸው እንጀራ በወቅቱ ወደ ማሰልጠኛ ተቋሙ ለቃለ ምልልስ የሄዱ የፕሬስ ድርጅት ባልደረባ ጓደኛቸው ቀድሞውንም የፎቶ ማንሳት ችሎታቸውንና ፍላጎታቸውን ይረዱ ስለነበር "አንተ እዚህ ምን ትሰራለህ ? ለምን እኛ መስሪያ ቤት ሄደህ አትቀጠርም? " አሏቸው። ሃሳቡን ተቀብለው በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በ1971 ዓ.ም መጡ።

" በወቅቱ ወደ ተቋሙ ስመጣ ሁሌም እስከ አሁንም ድረስ በምታወቅበት ዝነጣ ዘንጬ። ከረቫት አስሬ ነበር፤ የወቅቱ የስራ ኃላፊም ሲያዩኝ በጣም ደንግጠው" ስራው አለ ነገር ግን አንተን ሳይህ የእኛ ደመወዝ የሚበቃህ አይመስለኝም" አሉኝ፤ ስንት ነው ብዬ ስጠይቃቸው 153 ብር አሉኝ፤ በጣም ደስ ብሎኝ "የመንግስት ደመወዝና የቤተ ክህነት ምግብ ተለምኖ የሚበላ ነው" አልኳቸው በጣም ተገርመው በል እሺ አሉና፤ አንዳንድ በሙያው ዙሪያ ያሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀመሩ። በወቅቱ ግን ሙያውን እንዲሁ ልወቀው ልስራበት እንጂ በእውቀት ያልተደገፈ ስለነበር የጠየቁኝን ጥያቄ መመለስ አልቻልኩም" ይላሉ አቶ ክንፈሚካኤል ወደ ፕሬስ የመጡበትን አጋጣሚ እያስታወሱ።

በወቅቱ እኛ የፈተኗቸው የስራ ኃላፊ ዝም ብለው ሊሸኟቸው ወይንም ደግሞ አይ ፈተናውን አላለፍክምና መስራት አትችልም ሊሏቸው አልፈቀዱም። ይልቁንም አንተ ወጣት ነህ የሙያው ፍቅርና የመስራት ፍላጎት ያለህ በመሆኑ ከእኛ ጋር እዚሁ ቆይተህ የነጻ አገልግሎት ትሰለጥናለህ በማለት የእንጀራ በራቸውን እንደከፈቱላቸው ይናገራሉ። አቶ ክንፈሚካኤልም እድሉን ማጣት ስላልፈለጉ ተስማምተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በወቅቱ አጠራሩ ከማስታወቂያ መምሪያ ጋር ስራቸውን ጀመሩ።

" ........የሚገርመው ነገር ስልጠናውን እያገኘው ስራውን እየሰራሁ ሙሉ በሙሉ ስለሙያው ለማወቅ አጭር ጊዜ ብቻ ነበር የወሰደብኝ። ኃላፊው ጠይቀውኝ ያልመለስኳቸውን ጥያቄዎች ሁሉ በስራ ላይ አወቅኋቸው። በዚህም በጣም ደስ አለኝ ይበልጥ ወደሙያው ተሳብኩ የመስራት ፍላጎቴ ጉጉቴ ጨመረ " ይላሉ ወቅቱን ሲያስታውሱት።

ተቋሙም የካሜራ ባለሙያዎችን ለመቅጠር ማስታወቂያ አወጣ፤ ወጣቱ ክንፈሚካኤልና አንድ ሌላ ጓደኛቸው ፈተናውን ወስደው በጥሩ ሁኔታ አለፉና በ 153 ብር የወር ደመወዝ ስራው ጀመሩት። ለወጣቱ ክንፈሚካኤል ከአለቃቸው ዘንድ እንዲህ የሚል ሃሳብ ቀረበላቸው " እኛ አንተን የቀጠርነህ ለጦር ሜዳ ነው ለዚህ ፈቃደኛ ነህ ወይ የሚል"፤ የወጣቱ ክንፈሚካኤል መልስም "ለአገሬ በሙያዬ እዘምታለሁ" የሚል ሆነ።

ወጣቱ ክንፈሚካኤል በወቅቱ አገሪቱ ከወያኔ ቡድን ጋር እያደረገች ያለውን ጦርነት በቅርበት ይከታተሉ ነበር ጦርነቱም እጅግ ስቧቸዋል ለአገራቸው ደጀን ለመሆንም በውስጣቸው ያለው የአገር ፍቅር ስሜት ሲኮረኩራቸውም ከርሟል፤ ይህንን እድል ሲያገኙ ደግሞ ምኞታቸው ምሉዕ ሆነላቸው እጅግ በጣም እንደተደሰቱ በአንደበታቸው ይናገራሉ።

".......ወቅቱ ጦርነቱ የተፋፋመበት እነ ከረንና ሌሎች አካባቢዎች የተለቀቁበት ስለነበር ሬዲዮው ሁሉ የድል ዜና ነው የሚያሰማው ፕሮግራሞች ሁሉ የጦር ሜዳ ናቸው፤ ይህ ደግሞ በጣም ልብ የሚያሞቅ ከመሆኑ የተነሳ እኔና ጓደኛዬ ድምጹን በቴፕ ካሴት እየቀዳን ደጋግመን እንሰማው ነበር፤ ይህ ደግሞ ውስጤ የጦር ሜዳ ቃና እንዲቀር በቃ ምን ልበልሽ አዲስ አበባ ተቀመጥኩ እንጂ ልቤም መንፈሴም ሁሉ ነገሬ ጦር ሜዳ ነበር። ልክ ስራዬን ከተፈራረምኩ በኋላ ይህንን ስሰማ በጣም ደስ አለኝ" ይላሉ።

የሚያዚያ መጀመሪያ 1971 ዓ.ም የኮንትራት ቅጥራቸውን የተፈራረሙት ወጣቱ ክንፈሚካኤል በዛው ወር መጨረሻ በደስታና በሙሉ ልብ በአንቶኖቭ አውሮፕላን ተጭኖ ወደ አስመራ ሆነ ጉዞው።

እንግዲ ከከተማ ወጥተው የማያውቁት ጦር ሜዳንም በሬዲዮ እንጂ በአካል ያላዩት ወጣቱ ክንፈሚካኤል ገና አንቶኖቭ አውሮፕላኑ ላይ ሲወጡ ድምጹ የፈጠረባቸውን መረበሽና መደናገጥ ያስታውሳሉ። በጣም ለጆሯቸው ስለከበዳቸውም ሶፍት ጠቅጥቀው መጓዛቸውን ይናገራሉ። በጣም የሚያስቀው ነገር ደግሞ አስመራ ከተማ ደርሰው ከአውሮፕላኑ ሲወርዱ የጠቀጠቁት ሶፍት ወደ ጆሯቸው ዘልቆ ገብቶ ብዙ ችግር መፍጠሩና በኋላም አንድ ሀምሳ አለቃ ወታደር እንዳወጣላቸው እየሳቁ ይናገራሉ።

ጦርነት ሲቪል ሆነ ወታደር ሁሉን የማይመርጥ ጠላትን ነቅቶ መጠበቅ የሚያስፈልገው ክስተት መሆኑ ስፍራው ላይ ሲደርሱ በቦታው ከነበሩ የጦር አመራሮች መልዕክት ተላለፈ፤ በሌላ በኩል ማንም ሰው የወታደር ልብስ ሳይለብስ በሲቪል ልብስ መንቀሳቀስም ከባድ መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል ተነገረ። ይህንን ተከትሎም ለሁሉም የወታደር ልብስ ተሰጠ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ወጣቱ የፎቶግራፍ ባለሙያ ከልብሱ ጋር አብሮ የሚሄድ ቀበቶ አልተሰጣቸውም። እርሳቸውም ነገሬ አላሉት ለምን አልተሰጠኝም ብለውም አልጠየቁም።

".......በወቅቱ አስመራ ከተማ ሰዓት እላፊ ነበር። እኔ ደግሞ የወታደሩን ልብስ ለብሼ በከተማዋ እንቀሳቀሳለሁ በዚህ መካከል ፖሊስ ያዘኝና አስቆመኝ፤ ቀበቶ ለምን እንዳላደረኩ ጠየቀኝ። በወቅቱ ግን መልስ አልነበረኝም። ፖሊሱም ወደ ህግ አቀርበዋለሁ ምክንያቱም መንግስት የቀበቶ ችግር ሳይኖርበት ለምን ቀበቶ ማድረግ አልቻልክም በማለት ብዙ ችግር ተፈጠረ። አለማወቅ መሆኑን በመናገር ይቅርታ በመጠየቅና ሌላ ጓደኛዬም የራሱን ቀበቶ አውልቆ ሰጥቶኝ ወደ ካምፔ ሄድኩ" ይላሉ።

ኸረ ጦር ሜዳ እንዲህ ከባድ ከሆነማ ልመለስ አላሉም ? ብዬ ስጠይቃቸው? አቶ ክንፈሚካኤል ".....ማ እኔ ..... እኔ እኮ ተወልጄ ነፍስ ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ስለ አገር ፍቅርና ስለ ሃይማኖት ሲነገረኝ ስለ ባንዲራ ክብር ጠዋት ማታ ስመከር የኖርኩ ነኝ፤ በሃይማኖትና በአገሬ ምንም ቀልድ አላውቅም፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሁሌም ቢሆን ቁስሌ ነው" ነበር ያሉኝ ።

ጦር ሜዳን መቀላቀል ለብዙዎች ቀላል አይደለም አዎ ለአቶ ክንፈሚካኤልም ገና ከጅምሩ ቀላል አልሆነላቸውም፤ በተለይም ወታደራዊ ህግና ደንብን ማወቅ አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል። በዚህ በኩል ያጋጠማቸውን ሲናገሩም " ጦር ሜዳ በደረስኩ ትንሽ ቀናት ውስጥ አንድ ትልቅ ወታደራዊ ጀነራል ጋር በመሄድ ሪፖርት እንዳደርግ ተነገረኝ፤ እኔም የአካባቢውን በረሃማነት መቋቋም አቅቶኝ ስለነበር ብዙውን ጊዜ ከወገቤ በላይ ራቁቴን ነበር የምሆነው፤ ልክ እንደዛው እንዳለሁ ወደጀነራሉ "አቤት" ብዬ ሄድኩ በወቅቱ ግን የገጠመኝ ነገር እጅግ አስደንጋጭ ነበር፤ ጀነራሉ በጣም ከመደንገጣቸው የተነሳ ልክ እንዳዩኝ ምንድነው ብለው በከፍተኛ ቁጣ በትረ መኮንናቸውን በመወርወር አይኔን ሊመቱኝ ሲሉ ለጥቂት ተረፍኩ፤ ኋላ ላይ ግን አለቃ ፊት በተለይም ወታደራዊ መኮንኖች ጋር ሲገባ ትልቅ ስነ ስርዓት እንደሚያስፈልግ ነግረው ሸኙኝ "በማለት የገጠማቸውን ያስታውሳሉ።

በባህሪያቸው ስራ ፈተው መቀመጥ የማይፈልጉት ወይም የማይወዱት አቶ ክንፈሚካኤልን ካስቸገራቸው የጦር ሜዳ ኑሮ መካከል ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ የታለ ጠመንጃህ የሚለው ጥያቄ ነበር፤ እርሳቸው ደግሞ ጥሎባቸው በፍጹም ጠመንጃ መያዝን አልፈለጉም፤ ነገር ግን ፖሊሶች እያስቆሙ ጋዜጠኛ መሆናቸውን እንኳን ቢገልጹላቸው በፍጹም ጠመንጃ መያዝ አለብህ ብለው በማስገደዳቸው በቃ ጠመንጃ ስጡኝ በማለት ጠየቁ ኋላም ጠመንጃው ተሰጥቷቸው ታጥቀው መንቀሳቀስ ጀመሩ። ነገር ግን ለመንቀሳቀስ ብዙም ስላልተመቻቸው ብሎም ክብደቱን መቻል ስላቃታቸው ከጠመንጃው ጋር ብዙ መዝለቅን አልፈለጉም ወዲያው አስረከቡ።

ይህ አለማወቃቸው እንዲሁም ስራ ፈትቼ መቀመጥ የለብኝም የሚለው መንፈሳቸው ለሌላ ለዛውም ከባድ ለሆነ ስህተትና ከስህተትም በላይ ደግሞ ህይወትን ለማሳጣት በሚችል አደጋ ውስጥ ጨምሯቸው እንደነበር ያስታውሳሉ፤ አቶ ክንፈሚካኤል ሲናገሩ "...... በአንድ ወቅት ናቅፋን ለመያዝ ጋሬጣ የሚሆኑትን በርካታ ተራሮች በድማሚት ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ የጦር ግንባር መሃንዲሶች ሲሄዱ በአጋጣሚ አንድ ቦታ ቆመው አገኘኋቸው፤ የት ልትሄዱ ነው ? ስላቸው ግንባር አሉኝ፤ እኔም አብሬያችሁ እሄዳለሁ በማለት መኪና ውስጥ ገባሁ። ቦታው ላይ የሚሰሩትን በሙሉ ሲሰሩ እኔም አንዴ በልቤ እየተደፋሁ ሌላ ጊዜም እነሱ የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ እያደረኩ ቆየሁ በመጨረሻ አንድ ወታደር ወደእኔ መጣና ማንነቴን ጠየቀኝ መጀመሪያ ላይ በንግግር ሳንግባባ ሰውየው ትንሽ ቢናደድም በኋላ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር መምጣቴን ስነግረው ማነው እዚህ ቦታ እንድትገባ የፈቀደልህ? ሲልም ጠየቀኝ ማንንም ሳላስፈቅድ ወይም ሳልናገር መምጣቴን ተናገርኩ ወታደሩ ይበልጡኑ ተናደደ፤ አክሎም ቦታው የጨዋታ እንዳልሆነና በየደቂቃው በየሰከንዱ የሰው ልጅ ህይወት የሚገበርበት መሆኑን

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



በመግለጽ ሁለተኛ መሰል ስህተት እንዳልሰራ አስጠንቅቆኝ ወደመጣሁበት ግብረ ሃይል እንድሄድ ሸኘኝ" ይህ በጣም ይገርመኛልም አልረሳውም ይላሉ።

አቶ ክንፈሚካኤል ወቅቱን ሲያስታውሱ በጣም ከሚቆጫቸው ነገር መካከል እሳቸውና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ያነሷቸው ፎቶግራፎች ተንቀሳቃሽ ምስሎች (ቪዲዮዎች) ታሪክ ሆነው ለተቋማቱ መሰጠት አለመቻላቸው ነው።"........... በወቅቱ እኛ ከዚህ ፊልም ይዘን ሄደናል እዛ ስንደርስ የያዝነውን ፊልም አስረከብን፤ እንደገና ወደስራ ስንወጣ የሚስጥር ወረቀትና የፊልም መቆጣጠሪያ ይሰጠናል፤ በወቅቱም 20 ፊልም ቢሰጥ 15ቱን ከተጠቀምን 5ቱን በሰነድ ይመለሳል። ምናልባት እነዛ ምስሎች በየተቋማቱ ቢቀመጡ ስንት የአገር ታሪክ ይወጣቸው ነበር። ብዙ መረጃም እዛው ቀረ ይህ በጣም ይቆጨኛል " ይላሉ።

አቶ ክንፈሚካኤል ከ 1971 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ ጦርነቶች ላይ ተካፍለዋል፤ በ1971 ዓ.ም ናቅፋ በር። በ 1972 ዓ.ም አልጌና። 1973 ከ11 ኛ ክፍለ ጦር ጋር በገላዴን ጎህና በዴሜር ጆክ ላይ በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ የተማረኩትን ንብረቶች በሙሉ በፎቶ ካሜራቸው ታሪክ አድርገው ማኖር ችለዋል። የአቶ ክንፈሚካኤል የጦር ሜዳ ውሎ ይህ ብቻ አይደለም 1974 ሙሉን አመት ቀይ ኮከብ ዘመቻ ላይ ነው የቆዩት፤ በ 1978 ዓ.ም ናቅፋ ላይ ባህረ ነጋሽ ዘመቻን በታሪክ አስቀርተዋል። እነዚህ ሁሉ አልፈውም ቢሆን አገራችንም ከጦርነት አላረፈችምና እርሳቸውም ከጦር ሜዳ ጉዞ አልቦዘኑም። በ1992 ዓ.ም የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሲቀሰቀስ ወደባድመና ቡሬ በመጓዝ ታሪክን መሰነድ ችለዋል።

"........አገሬን እወዳለሁ ለባንዲራዬም እሞታለሁ ስል ምስክሮቼ እነዚህ የጦር ሜዳ ስራዎቼ ናቸው። በየትኛውም የጋዜጠኝነትም ሆኖ የፎቶ ሪፖርተርነት ታሪክ ውስጥ እንደ እኔ አገሩን ጦር ሜዳ ሄዶ ያገለገለ የለም፤ ስድስት ጊዜ ጦር ሜዳ መሄዴ በጣም ያኮራኛል፤ በእነዚህ ሁሉ ጊዜያት ምንም ዓይነት የመቁሰል አደጋ አልገጠመኝም፤ ይህ የሆነው ግን በእድልና በአጋጣሚ እንጂ ሁኔታዎች ምቹ ስለነበሩ ወይም ራሴን ስለጠበኩ አይደለም፤ በነገራችን ላይ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅትም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ ሞቷል፤ ከዛ በፊትም በ1972 ዓ.ም የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ አውሮፕላን ሲቃጠል አብሮ ተቃጥሏል ሌላም ሌላም ብዙ ታሪክ አለ " ይላሉ።

"......የሚናፍቀኝ ሰላም ነው ለምሳሌ በ1976 ዓ.ም ላይ እኔ የነበርኩበት ጦር 505 አልጌና ላይ ሙሉ በሙሉ ነው የተደመሰሰው፤ ግብረ ሃይል ተደመሰሰ ሲባል ቀላል እንዳይመስልሽ በጣም ከባድ ነው፤ ብዙ ሰው በርካታ መሳሪያ ምን ቅጡ በጣም ያሳዝናል፤ በሶማሌ ጦርነትም ወቅት ብዙ አልቀናል፤ ይኸው እስከ ዛሬ ድረስ እያለቅን ነው። ነገር ግን ከጦርነት የምናተርፈው ወይም የምናገኘው አንዳችም ነገር የለም፤ አሁንም ቢሆን መንግስት የገባንበትን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ እመኛለሁ። ምክንያቱም እነሱ ምንም ይሁኑ ምን አንድ ጊዜ በደም ተጋምደናል ይህንን ደግሞ መካድም ሆነ መሰረዝ በጣም ከባድ ነው። በመሆኑም ሁሉም ነገር ሰላም ሆኖ የሚያበቃበትን ጊዜ እናፍቃለሁ፤ በዚሁ ከቀጠልን ግን ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ግብጽና ሱዳን ጭዳ ነው የምንሆነው "ይላሉ።

አንጋፋው የፎቶ ሪፖርተር አቶ ክንፈሚካኤልም እነዚህ ሁሉ የጦር ሜዳ ተሳትፎዎችን ከማድረግ ባሻገር ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ከአገሪቱ ቁንጮ ባለሰልጣናት ጋር አለምን የመዞር እድል ያገኙ ስለመሆናቸው በራሳቸው እንደበት ይናገራሉ።

"......እኔ እንግዲህ በፎቶ ጋዜጠኝነት ስራ ዘመኔ ከ 29 በላይ የአለም አገራትን የማየት እድሉን አግኝቻለሁ፤ አፍሪካ ውስጥ ከጅቡቱ በቀር ሰሜኑንም ደቡቡንም ምስራቁንም ሁሉንም አይቻለሁ፤ አንዳንዶቹ እንደውም ከአምስት ጊዜ በላይ አይቻቸዋለሁ። አሜሪካን ጣሊያን ፈረንሳይ እና ሌሎችም አገራትንም አይቻቸዋለሁ። ከዚህ በላይ ግን እንዲታወቅልኝ የምፈልገው እነዚህ ሁሉ አገሮች ሄጄ የስራ ግዳጄን ተወጥቼ ከመምጣት ባሻገር አንድም ቀን ጠፍቼ እቀራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም፤ ልሞክረውም አልፈለኩም፤ ምክንያቱም አገሬን ከልቤ ማፍቀሬ ነው" በማለት ይናገራሉ።

በተመሳሳይ ኢትዮጵያን ከናቅፋ ጀምረው እስከ ሞያሌ፤ ከሞያሌ በዶሎ በኩል ኬንያ ማንዴራ፤ ከማንዴራ ጉባ ድረስ በጠቅላላው በአራቱም መዓዘን የአገሪቱን ጠረፍ አካለዋል። በዚህ የስራ ጊዜያቸው ደግሞ ያሳደጓቸውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አብዝተው በፎቶ ሪፖርተርነት አገልግለዋል። ብዙ ታሪካዊና ዘመን የማይሽራቸውን ፎቶግራፎች ሰንደዋል። በዚህ ስራቸውም አንጋፋ የሚል ማዕረግን ያገኙ ታላቅ ባለሙያ ስለመሆናቸው ብዙዎች ይመሰክራሉ።

ስራቸውን ለመስራት በተንቀሳቀሱባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች የተለያዩ አደጋዎች አጋጥሟቸዋል ለምሳሌ በሄሊኮፕተር ተከስክሰዋል። ባህርዳር ላይ በመኪና ተገልብጠዋል። በ1997 ዓ.ም በነበረው አገራዊ ምርጫ ወቅትም በደረሰባቸው አደጋ እግራቸው መሰበሩን ይናገራሉ። ይህ ግን ለአገሬ ለሙያዬ ፍቅርና ክብር የከፈልኩት ዋጋ በመሆኑ ደስተኛ ነኝ ይላሉ።

አሜሪካን አገር ሄደው የሆነ የገጠሞት ነገር አለ ይባላልና ስለእሱ አጫውቱኝ ስላቸውም፤ በሳቅ በትዝታ የኋሊት እየሄዱ ".....አዎ አሜሪካን አገር ትልቅ ገጠመኝ አለኝ። አሜሪካን ኒውዮርክ ከሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ነበር የሄድኩት በወቅቱ ስብሰባው ይካሄድ የነበረበት አዳራሽ ከስፋቱ የተነሳ ሰውን ከሰው መለየት ከባድ ነበር። እኔ የያዝኩት ካሜራ ደግሞ ሃያ ሚሊ ሜትር (የዓይን ብርሃናችንን) ያህል ብቻ የምትረዝም ናት፤ በዚህ ርዝመት ጠቅላይ ሚኒስትሩን አግኝቶ ፎቶ ማንሳት እጅግ ፈታኝ ሆነ። መሪዎቹ ስብሰባቸውን ጨርሰው እስከሚወጡ ድረስ የረባ ስራ አልሰራሁም። ይህም በጣም አሳስቦኛል። ኋላም አብረውኝ ያሉት የሙያ ባልደረቦቼ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ ተወካይ ወደሆኑት ግለሰብ ስልክ ፈልጌ እንድደውል አዘዙኝ፤ ተስማማሁና ስልክ ፍለጋ ሄድኩ፤ በወቅቱ ሰውየውንም በስልክ ካለማግኘቴም በላይ ስመጣ ሌላ ዱብዳ ገጠመኝ " ይላሉ።

ስልክ ፍለጋ የሄዱት አቶ ክንፈሚካኤል ሲመለሱ ጓደኞቻቸውን በተዋቸው ቦታ ላይ አላገኟቸውም በተመደበላቸው መኪና ጥለዋቸው ሄደዋል። በዚህን ጊዜ በሰው አገር ወዴት ልሂድ የሚለው ድንጋጤ በከፍተኛ ሁኔታ ይይዛቸዋል።

".......በወቅቱ ከጓደኞቼ የታዘዝኩትን ስልክ ፈልጎ የመደወል ሃላፊነት ለመወጣት ነበር የሄድኩት ስመጣ ግን ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጽህፈት ቤት ንግግር ሊያደርጉ ነው በሚል ሁሉም ጥለውኝ ሄደዋል። በህይወቴ እንደዛ አይነት ድንጋጤ የደነገጥኩበትን ወቅት አላስታውሰም። ወዴት ልሂድ የሚለው ነገር ወጥሮ ያዘኝ ወይስ አገሩን ከዳ ጠፋ ልባል ነው። ብዬ ተጨነኩ በኋላም ከብዙ ማሰብ በኋላ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጠየኳቸው። እነሱም ታክሲ ይዤ ወደተባለው ቦታ መሄድ እንደምችል አመላከቱኝ፤ በዛው መሰረት ሄድኩ ግን አላገኘኋቸውም። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ንግግር አላደረጉም። ይባስ ብዬ እዛ ሳጣቸው እንባ አውጥቼ አለቀስኩ በኋላ ግን ጓደኞቼም ከሄዱበት መጥተው ትልቅ ይቅርታ ጠይቀውኝ አብረን መጣን" በማለት ኒውዮርክ ላይ የገጠማቸውንና እጅግ ያስደነገጣቸውን አጋጣሚ ይናገራሉ።

አንጋፋው የፎቶ ጋዜጠኛ አቶ ክንፈሚካኤል በሰዎች ዘንድ ከሚታወቁበት አንዱ እጅግ ዘንጣፋ ቁመና ያላቸው በዛው ልክ በበዓል በስራ ቀን አንድ አይነት አለባበስ የሚያዘወትሩ ዘናጭ መሆናቸው ነው። ይህ ደግሞ በሚንቀሳቀሱባቸው (በአገር ውስጥም ሆነ ውጭ አገር) ከሌሎች በተለየ መልኩ እንዲታዩ የጠየቁትን የሚፈልጉትን ሁሉ በፍጥነት እንዲያገኙም ያግዛቸው ነበር ።

ቁመናዬ በጣም ይገርምሻል ብዙ ነገሮችን ለማሳካት ጠቅሞኛል፤ በእርግጥ በማህበራዊ ግንኙነቴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖም ቀላል አይደለም ይላሉ። በተለይም የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ላይ ስገኝ ሁሉም ነገር ለእኔ ምቹ ነበር፤ ሌሎች ጋዜጠኞች የተከለከሉበት ቦታ ሁሉ ገብቼ ፎቶ ለማንሳትም አልቸገርም በማለት ያስታውሳሉ።

"......ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ስራ የሄድኩት በደርግ ጊዜ ከነበሩት ጉምቱ ባለስልጣን ከአቶ ፍቅረስላሴ ወግደረስ ጋር ነበር፤ የሄድነው ዚምባቤ ሲሆን መሪ ሞቶ ለቀብር ነበር፤ ግን ከላይ ኒውዮርክ ላይ እንደገጠመኝ አይነት ሁኔታ አጋጠመኝ አዳራሹ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ የእኔ ካሜራ እዛ ውስጥ ያለን ነገር በፎቶ ማስቀረት አቶ ፍቅረ ስላሴንም ማንሳት እንደማልችል ተረዳሁ፤ እሳቸውን ሳላነሳ ከመጣሁ ደግሞ በአለቆቼ ዘንድ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ገመትኩ፤ በመሆኑም ቁመናዬን ዝነጣዬን መጠቀም አለብኝ ብዬ ወሰንኩና ካሜራዬን በኮት ኪሴ ውስጥ ደብቄ መሪዎች በሚገቡበት በር ቀጥ ብዬ ገባሁ እንኳን የት ነህ ብሎ ሊጠይቁኝ ቀርቶ ልክ እንደ አንድ አገር መሪ ተቀበሉኝ። የአዳራሹ በር ተዘግቶ ንግግር ከተጀመረ በኋላም ካሜራዬን በማውጣት የምፈልገውን ሁሉ በፎቶግራፍ አስቀርቼ በገባሁበት በር ወጣሁ። እናም ቁመናዬን ተጠቀምኩበት ማለት አይደል " በማለት ይናገራሉ።

እዚሁ ላይ ግን ሌላ የገጠመኝን ነገር ላጫውትሽ የሚሉት አቶ ክንፈሚካኤል ይህ የቀብር ፕሮግራም ሳይጠናቀቅ ከተማዋ በቦንብ ፍንዳታ ራደች በዚህ ጊዜ መሪዎቹም ተሸበሩ ሁሉም ግራ ተጋባ በቶሎ መሪዎቹን ለማስወጣት ተፍ ተፍ ማለት ተጀመረ በዚህ ጊዜ እኔም ምን ልሆን ነው የሚል ስጋት ውስጥ ገባሁ በኋላ ግን አቶ ፍቅረስላሴ ወግደረስና ፕሮቶኮላቸው አምባሳደሮች ወደ መኪና ሲገቡ አየሁ እኔም በድፍረት ከእናንተ ጋር ነው የመጣሁት ጥላችሁኝ ልትሄዱ ነው ብዬ ስጣራ ሲያዩኝ እውነትም ከእነሱ ጋር የመጣሁ ባለስልጣን ነበር የመሰልኳቸው በል ቶሎ ወደመኪና ግባ ብለው ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ወሰዱኝ። ከዛማ እኔን ማን ይቻለኝ በማለት በትልቅ ሳቅ ውስጥ ሆነው ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

ይህንን በሶስት መንግስት ውስጥ ያለፈን ታሪካቸውን አልፎም የትወልድ ማስተማሪያ ሊሆኑ የሚችሉ የስራ ዘመን ቆይታቸውን ደግሞ በመጽሃፍ መልክ አዘጋጅቶ ማቅረብ ህልማቸው ቢሆንም እስከ አሁን ግን ምቹ ሁኔታዎችን አላገኙም። ምናልባት ታሪኩ የሳበው ለትውልድ ቢተላለፍ ይጠቅማል የሚል አካል ካገኙም አብረው ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውንም ነግረውኛል።

የህይወት ዘመናቸውን ከግማሽ በላይ ካገለገሉበት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጡረታ ከተሰናበቱ በኋላ "አናዱሉ" በተባለ የዜና አገልግሎት ተቋም ውስጥ ገብተው በፎቶ ሪፖርተርነት ለአንድ አመት ያህል መልካም የሚባል የስራ ጊዜና ብዙ ልምዶችን እንዳካበቱ ይናገራሉ።

አቶ ክንፈሚካኤል ጉረኛ ናቸው ከአለባበሳቸው ጀምሮ ለሚሏቸውም "…. እኔ ጉረኛ አይደለሁም፤ እንደውም በጓደኞቼ በሚቀርቡኝ ሰዎች ዘንድ ተጫዋች ተግባቢ ነኝ፤ ነገር ግን የሚመስለኝን የማደርግ ካልመሰለኝ የምተው በራሴ መንገድ የምሄድ ሰው ነኝ። ራስን መጠበቅ ንጹህ ሆኖ መታየት ከጉራ ከተቆጠረ ደግሞ ምንም ማድረግ አይቻልም"።

አቶ ክንፈሚካኤል ለስራቸው ለሙያቸው የከፈሉት መስዋዕትነት ብዙ ነው በዚህም የተነሳ አንዲት ልጅ ከመውለድ የዘለለ የቤተሰብ ህይወት የላቸውም።

**ምስጋና**

ከልጅነት እስከ እውቀት እድሜዬን ከሰጠሁበት የኢትዮጵያ ፕሬስ ደርጅት በጣም ታሪካዊ የሚባሉ ስራዎችን ከሰራሁበት ተቋሜ አወጣጤ ባያምርም አልናደድም። ምክንያቱም ዘመን ተሻጋሪ የሆነ ታሪክ መስራትም ሆነ ለትውልድ ማቆየት የቻልኩት እዛ ተቋም ላይ በመስራቴና እድሉን በማግኘቴ ነው።

አሁን ደግሞ እንደ ቤቴ የምወደውን ተቋም መለስ ብዬ ሳየው እጅግ እደሰታለሁ አዳዲስና ወጣት አመራሮች መጥተውለታል ብዙ የለውጥ ስራዎች አሉ። ጋዜጣው ላይ የሚሰሩ ስራዎች ጥሩ ናቸው የፎቶ አጠቃቀም ከወትሮው እጅግ በጣም ተለይቷል ሳቢም ሆኗል። የእለቱን ሁነቶች እንደ ድሮው ነገላይ መጠበቅ ቀርቷል ቶሎ ቶሎ ዜናዎች በማህበራዊ ትስስር ገጹ ይለቀቃሉ እድሜ ሰጥቶኝ ይህንን የተቋሙን ለውጥ በማየቴ በጣም ደስተኛ ነኝ።

እኔንና መሰሎቼንም ከተረሳንበት አስታውሰው ምንም ዓይነት ብጣቂ ወረቀት ሳናገኝ ከተሸኘንበት ጊዜ አስታውሰው የምስክር ወረቀት ሰጥተውናል ይህ በህይወቴ ከማልረሳቸው የደስታ ቀኖቼ እንደ አንዱ አድርጌ ይዤዋለሁ በማለት ይናገራሉ።

ከዚህ ውጪ ወጣት ጋዜጠኞችም ሆኑ ፎቶ ሪፖርተሮች በተለይም አገራችሁን ውደዱ የምትሰሩበትን ተቋም አክብሩ ስራችሁ ላይ ትጉ ሁኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች እጃችሁ የሚገቡ የአገርና የተቋም ሚስጥሮችን ጠብቁ። ከምንም በላይ ደግሞ ተቋማችሁን ወክላችሁ ወደስራ ስትሰማሩ የግል ንጽህናችሁን ጠብቁ በማለትም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# “የቅርስ ቀን”ን- ማክበር ለምን አስፈለገ?

**ዳግም ከበደ**

የዓለም የቅርስ ቀን በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) አማካኝነት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሚያዚያ 18 በየዓመቱ ይከበራል። ይህ በዓል በዘመናት ሂደት ውስጥ የሰው ልጅ ያሳረፈውን የስልጣኔ አሻራና ሃብት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለማስተዋወቅ ከመዋሉም በላይ ለትውልድ ለማስተላለፍና ለሃብቶቹ የሚሰጠውን ክብር ከፍ ለማድረግ ልዩ አጋጣሚን እንደሚፈጥር ይታመንበታል። በተለይ የቀደሙት ትውልዶች አኗኗር፣ ስልጣኔና እውቀት ምን ይመስል እንደነበር ምስክር የሚሆኑ ቁሳዊና ባህላዊ ሃብቶችን ለማስተዋወቅ ቀኑ ከወትሮው በተለየ አስፈላጊ ይሆናል።

ኢትዮጵያ በዓለም ስልጣኔ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ካበረከቱ አገራት ተርታ በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። የባህል፣ የታሪክ፣ የአገረ መንግስት ምስረታና የጥንታዊ ስልጣኔ ምስክር የሆኑ አስደናቂ ቅርሶች፣ ሙዚየሞችና ልዩ ልዩ ታሪካዊ ሃብቶች መገኛም ጭምር ነች። በዚህ ምክንያት አርኪዮሎጂስቶች፣ ጎብኚዎችና በቱሪዝም፣ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ላይ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ ትኩረት ያደርጉባታል። ይሁን እንጂ የጥንታዊ ስልጣኔና ጥንታዊ ሃብቶች መገኛነቷን ያህል በመላው ዓለም ሃብቶቹን ለማስተዋወቅ፣ ለማልማትና ከዚያም የሚገኘውን ምጣኔ ሃብት በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ ስትሆን አይታይም።

ለዚህ እንደ ችግር ተደርጎ የሚወሰደው ቀደም ባሉት ጊዜያት መንግስት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ በስፋት ያለመስራትና ጠቀሜታውን ያለማጉላት ነበር። ከዚያም ባለፈ የባህል፣ የታሪክና የስልጣኔ ምስክር ተደርገው የሚጠቀሱ በመላው አገሪቱ የሚገኙ ሃብቶችን በእውቀትና በልዩ ጥንቃቄ የመምራት ችግር እንደነበርም ይታመናል።

አሁን በስልጣን ላይ ያለው አዲስ መንግስት ችግሩን ተገንዝቦ የቱሪዝም ዘርፉን በልዩ ትኩረት እና ጥንቃቄ ለመምራት ወስኖ እየሰራ ነው። ከአምስቱ ዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንደኛው እንዳደረገውና የታሪክ፣ የባህል፣ የቅርስ ጉዳዮችን የሚጠቀልለው ቱሪዝም በሁሉም አቅጣጫ እምርታ እንዲያሳይ የአደረጃጀት ለውጥ ማድረጉን አሳውቆ መስራት ውስጥ ከገባ ወራት ተቆጥረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት ተጠብቀው የቆዩት ቅርሶችን ከሚያስተዳድረው፣ ከሚጠብቀውና ከሚያለማው የቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ቅርስ ጥናት ጥበቃ ባለስልጣን ነው። ይህ መስሪያ ቤት በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በሚዳሰስ (ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ) እንዲሁም በማይዳሰሱ የባህልና የመንፈሳዊ ቅርሶች ዙሪያ ያሉ ማናቸውንም ቅርሶች ጠብቆ ለትውልድ የማሻገር ኃላፊነት አለበት። ከዚያ ባለፈ በመላው ዓለም እንዲታወቁና የቱሪስት መስህብ ከመሆን አልፈው ለአገር የምጣኔ ሃብት የጀርባ አጥንት እንዲሆኑ ኃላፊነት የተሰጠው መስሪያ ቤት እንደሆነ ይታወቃል።

ከእነዚህ ተግባርና ግዴታዎቹ መካከል ቀዳሚ የሆነው ዜጎችም ሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ ቅርሶች የማስተዋወቅ፣ ግንዛቤ የመፍጠርና ሁሉም ጥበቃ እንዲያደርጉለት የማድረግ ኃላፊነት ለመወጣት የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ እየሰራ መሆኑን መስሪያ ቤቱ አስታውቋል።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሱን መረጃ መሰረት ይህንን ግብ ለማሳካት በልዩ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ “የቅርስ ቀን” በአገር አቀፍ ደረጃ ማክበር ይጀመራል። የሚከበርበት ቁርጥ ቀን ይፋ ባይደረግም ይህ ሁነት በይፋ በየአመቱ ሲከበር በኢትዮጵያ ለሚገኙ ቅርሶች ልዩ ትኩረት ለመስጠትና ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው እንዲጎላ ለማድረግ ሰፊ እድል የሚፈጥር እንደሆነ ይናገራሉ።

“ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቅርስ ቀንን በግንዛቤ ፈጠራና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ታከብራለች” ያሉት የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እስካሁን ሲከበር የቆየው የሙዚየም ቀን ተብሎ እንደነበር ይናገራሉ።



ኢትዮጵያ በአይነትም በርካታ የቅርስ ሀብት ያላት በመሆኑና የቅርስ ቀንን ማክበር ስላለባት ቀኑን ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነም ይገልጻሉ። አገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት እንደመሆኗ፤ የቅርስ ቀኑን ከማክበር ባሻገር ቅርሶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ የቅርሶችን ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስችል የግንዛቤ ፈጠራ በመስራት በተለያዩ የንቅናቄ መርሃ ግብሮች እንደሚከበር ነው ያስታወቁት።

በዓለም ላይ ያሉ በቅርስነት የተመዘገቡ ኃብቶች በተገቢው መልኩ የሚተዋወቁት አገራት በሚገነቧቸው ጠንካራ የግንኙነት መስመሮች እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ በኩል የመገናኛ ብዙሃንና የፕሮሞሽን ተቋማት ለዚህ ትልቁን ድርሻ ይጫወታሉ። ይህን መስመር ተከትለው በእያንዳንዳችን ደጃፍ የሚደርሱት የማስተዋወቅና የመስህብ ስፍራነታቸውን ተደራሽ የማድረግ ስራዎች አብዛኛውን ጊዜ ስኬታማ ይሆናሉ። ከሁሉም አቅጣጫ ጎብኚዎች ወደ እነዚህ የስልጣኔ ምልክቶችና የዓለም ቅርሶች በመትመም የታሪኩ አካል ይሆናሉ። አገራቱም ይህን መሰረት አድርገው ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም ይፈጥራሉ።

ቀኑን ለማክበር በባለስልጣኑ በኩል በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶች የተመዘገቡበትን ቀን በመለየት የግንዛቤ ፈጠራ ለመስራት የኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ ተነድፎ እንቅስቃሴ መጀመሩንም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይፋ አድርጓል። ባለስልጣኑ እስካሁን ደካማ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ እንደነበረው የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ጠንካራ ኮሙዩኒኬሽን እንዲኖር ለማድረግ በአዲስ መልክ ለማደራጀት ስትራቴጂ ተነድፎ ምክክር እየተደረገበት እንደሆነም ያስረዳሉ።

የቅርስ ቀንን እንደማንኛውም አገር ማክበር ሳይሆን ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ግንዛቤ የሚፈጥሩ መልዕክቶች ተዘጋጅተው እንዲተላለፉ በማድረግ ቀኑ ይከበራል። አሁን ባለው ሁኔታም በርካታ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ከቦታቸው የተወሰዱና የጠፉ በመሆናቸው የሚመለከታቸው አካላት ክትትል እንዲያደርጉ የሚያስችል ሥራ እንደሚሰራ ምክትል ዳይሬክተሩ ለዝግጅት ክፍላችን አሳውቀዋል።

“በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ዙሪያ ወቅቱን የመጠነ የኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ መኖር መቻል አለበት” የሚሉት ምክትል ዋና ዳሬክተሩ፤ በቅርስ ውድመትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ አልፎ አልፎ የተሳሳቱና የተዛቡ ግንዛቤዎች በማህበራዊ ሚዲያ እንደሚሰራጩ ነው የሚናገሩት። እነዚህን ማስተካከልና ትክክለኛ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ ባለስልጣኑ ጠንካራ ኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ እንዲኖር እየሰራ መሆኑንም ያመለክታሉ።

ዩኔስኮ ቅርሶችን ከመጠበቅ አንጻር አንድ ባለድርሻ አካል ቢሆንም ዋናው ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ የተመዘገበውን ቅርስ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ እንዳለም ያስገነዝባሉ። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ በርካታ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ያስመዘገበች አገር እንደመሆኗ ለቅርሶቿ ደህንነት ቅድሚያ እንዲሰጥ እየተሰራ እንደሚገኝም ይናገራሉ።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ነች። ከ3 ሚሊዮን ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረው፤ “የሉሲ” ወይም ድንቅነሽ ቅሪተ አካል እንዲሁም የአረቢካ ቡና ዝርያ መገኛም ነች። የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ ጥቁር አባይም መነሻም ኢትዮጵያ ነው። የኤርታአሌ የእሳተ ገሞራ ሀይቅና የዓለማችን እጅግ ረባዳና ሞቃት ስፍራ ዳሎልም የሚገኙት በኢትዮጵያ ነው።

እነዚህ ብቻ አይደሉም። ኢትዮጵያ የንግስት ሳባ አገር ነች፣ የሙሴ ፅላትም/ ጽላተ ሙሴ/ የሚገኘውም በኢትዮጵያ ነው፤ በአክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን። ከእነዚህ ሌላ ለመዝናናት አመቺ የሆኑ በርካታ የስምጥ ሸለቆ ሃይቆችና ፍል ውኃዎች፣ እንዲሁም የዱር እንስሳት ፓርኮችና መጠበቂያዎች ይገኛሉ።

እንግዲህ፤ ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፤ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ አገር ለመሆን በቅታለች። በተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የበለፀገች፤ አያሌ የቱሪስት መስህብ ያላት ናት። እነዚህንም ቅርሶችን በዩኔስኮ መዝገብ በብዛት በማስመዝገብ ከአፍሪካ አገራት ቀዳሚዋ ብትሆንም የአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ግን የሚፈለገውን ያህል ወይም የሚገባውን ያህል አላደገም።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መንግስት የቱሪዝም ዘርፉ የኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት እንደሆነ በማመን ልዩ ትኩረት መስጠቱን አስታውቋል። በተግባር ሰፋፊ ልማቶችን፣ ፕሮጀክቶችን እያከናወነ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ታዲያ ይሄን መልካም አጋጣሚ መጠቀም ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በተለይ በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች በቱሪዝም ሆስፒታሊቲ ዘርፍ፣ በፕሮሞሽንና የገበያ ልማት ብሎም በአስጎብኚ ድርጅቶች ውስጥ በቀጥታ ሊሳተፉ ይገባል። የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ “ምድረ ቀደምት” አገራችንን ለመላው ዓለም ከፍ አድርጎ ማስተዋወቅ እንዲቻል ከማድረጉም ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ትርፉ ለአገር እድገት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ጥርጥር አይኖረውም።

ባለስልጣኑ በቅርብ ጊዜ ውስጥ “የኢትዮጵያ የቅርስ ቀን” በሚል በተለያዩ መርሃ ግብሮች ለማክበር ማሰቡ ደግሞ ተጨማሪ መነቃቃትን እንደሚሆን ይጠበቃል። በተለይ የቱሪዝም መስህብ የሆኑ ስፍራዎችን በልዩ ሁኔታ ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲይዝባቸው ለማድረግ ይረዳል።

በዋናነት ግን ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ሃብቶች ከሚገኝ ምጣኔ ሃብት ተጠቃሚ የምትሆንበት እድል እንዲጨምር በልዩ ሁኔታ የሚከበሩ ቀኖች ፋይዳቸው ከፍተኛ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ከኢትዮጵያ ያነሰ የመስህብና የቅርስ ስፍራ ያላቸው አገራት በስፋት ሃብቶቻቸውን ለማስተዋወቅ የተለያዩ ስልቶችን መንደፍ በመቻላቸውና ለተግባራዊነቱም በመስራታቸው የዚህ እድል ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ይሁን እንጂ “የቅርስ ቀን” ተብሎ ሲከበር ከዚህ ቀደም እንደሚደረገውና የስብሰባና ቲሸርት ህትመት አሊያም ግቡን ከመነሻው ያላወቀ የሁነት ዝግጅት ከሆነ አሁንም የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ አይችልም። ከላይ የባለስልጣን መስሪያቤቱ “የኮምኒኬሽንና የግንኙነት አወቃቀራችን ደካማ ነበር” በማለት ዳግም ለማዋቀር ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ነግሮናል። የማስተካከያ ስራው ሲተገበር የግንኙነት መስመሩን ዓለማቀፋዊ እንዲሆንና በብቁ ባለሙያዎች ሊመራ ይገባል የሚል እምነት አለን።

### እንደ መውጫ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም ቅርስነት በተመዘገቡ የኢትዮጵያ መስህቦች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደቀኑ ችግሮች እንዳሉ ይታመናል። በተለይ በሰሜኑ ክፍል በነበረው ጦርነት፣ አሁንም በተደቀነው ዓለመረጋጋትና ስጋት ምክንያት የላሊበላ፣ አክሱምና መሰል ቅርሶች ለጉዳት ተጋላጭ እየሆኑ ነው። ከዚህ መነሻ መሰል የቱሪዝም ዘርፉንና በውስጡ ያሉትን ሃብቶች የሚዘክሩና ሰፊ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ “የቅርስ ቀንን” የመሰሉ በዓላት ሲከበሩ ጉዳት የተጋረጠባቸው የመስህብ ስፍራዎች በሚመለከተው አካል ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህንን አጋጣሚ መጠቀምና ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ መከላከል የሚቻልበትን አጋጣሚም መፍጠር ይቻላል ብለን እናምናለን።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የጦር መኮንኖችን የበላው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ

ዋሰልኝ አየለ

ባለፈው ሳምንት ግንቦት ሰባትን አስታውሰናል። የግንቦት ወር የኢህአዴግና የደርግ ታሪክ ነው ማለት ይቻላል። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ብዙ ወጣቶች የተጨፈጨፉበት የዘመነ ኢህአዴግ ምርጫ የተደረገበት፣ ግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም በደርግ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የተደረገበትና ብዙ የጦር መኮንኖች የተረሸኑበት፣ ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከአገር ለቀው የወጡበት፣ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ የአገሪቱን ርዕሰ መዲና አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት።

ሌላው የሚያስገርመው ደግሞ የሁለቱም መንግሥት መሪዎች የተወለዱት በግንቦት ወር መሆኑ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የተወለዱት ግንቦት 19 ቀን 1933 ዓ.ም ሲሆን አቶ መለስ ዜናዊ ደግሞ የተወለዱት ግንቦት 1 ቀን 1947 ዓ.ም ነው።

ከእነዚህ የግንቦት ወር የደርግና የኢህአዴግ መንግሥታት ክስተቶች ለዛሬው የግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እና የግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ከአገር መውጣት እናስታውሳለን። የሻምበል ኢዮብ አባተ «ጀኔራሎቹ» መጽሐፍ እና ሌሎች ሰነዶች የመረጃ ምንጮቻችን ናቸው።



በግንቦት 1981 የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ በተወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያ ታላላቅ የጦር ጄነራሎቿን ያጣችው በዚህ ሳምንት ነበር፣

ግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም ሌተናንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ለጉብኝት ወደ ምስራቅ ጀርመን ሄዱ። በዕለቱም መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የመጨረሻው የአድማ ስብሳባ ቦታ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ግቢ ነበር።

ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ንጉሤ (የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም)፣ ሜጀር ጀኔራል ኃይሉ ገብረሚካኤል (የምድር ጦር ዋና አዛዥ)፣ ሜጀር ጀኔራል አምሃ ደስታ (የአየር ኃይል ዋና አዛዥ)፣ ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ (የባሕር ኃይል ዋና አዛዥ)፣ ሜጀር ጀኔራል ወርቁ ዘውዴ (የፖሊስ ሰራዊት ጠቅላይ አዛዥ)፣ ሜጀር ጀኔራል አብዱላሂ ዑመር (የአገር መከላከያ ሚኒስቴር አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ)፣ ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በላይ (የኢንዱስትሪ ሚኒስትር)፣ ሜጀር ጀኔራል አበራ አበበ (የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ)፣ ብርጋዴር ጀኔራል ተስፋዬ ትርፌ (በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ዘመቻ መኮንን)፣ ብርጋዴር ጀኔራል ደሳለኝ አበበ (የጦር ኃይሎች አካዳሚ ዋና አዛዥ)፣ ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም (በአገር መከላከያ ሚኒስቴር የእቅድና ፕሮግራም መምሪያ ኃላፊ) እና ሌሎች የጦሩ አባላት ከመከላከያ ሚኒስትሩ ቢሮ አጠገብ ባለው አነስተኛ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ተሰበሰቡ።

በስብሰባው ላይ የተገኙት ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት የጦሩ ባለስልጣናት ይሁኑ እንጂ ከየጦር ክፍሎቹ የተመለመሉት አዛዦችም የሚሰጣቸውን ጥዕዛዝ ለመፈፀም በተለያዩ አካባቢዎች ተዘጋጅተው ነበር። ለአብነት ያህልም፤ የ603ኛ ኮር መምሪያ ዋና አዛዥ ሜጀር ጀኔራል ዘውዴ ገብረየስ (ጎንደር)፣ የአየር ኃይል ምክትል ዋና አዛዥ ብርጋዴር ጀኔራል ሰለሞን በጋሻው (ደብረ ዘይት)፣ የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት ዋና አዛዥ ሜጀር ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ (አስመራ) እና ሌሎች የጦሩ አባላት ተጠቃሽ ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ መታወስ ያለበት አስቂኝ ድርጊት አለ። የመፈንቅለ መንግሥቱ ጠንሳሽና የአድመኞቹ ሰብሳቢ ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በላይ ወደስብሰባው የመጡት ዘግይተው ነበር። ወደ አዳራሹ ሲገቡ የሰብሳቢነቱን ቦታ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ንጉሤ ይዘውታል። ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ቦታውን መልቀቅ ሲገባቸው ዝም አሉ። ይባስ ብለውም ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ቦታውን የመልቀቅ አዝማሚያ ሳያሳዩ ስብሰባውን መምራት ቀጠሉ። መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የተሰበሰቡት የጦር አዛዦች እዚያው በዚያው ሌላ መፈንቅለ መንግሥት አደረጉ። ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በሁኔታው ተበሳጭተው ስብሰባውን ጥለው ወጥተው እጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ አድርገው መንጎራደድ ጀመሩ።

ሌላው ደግሞ በመፈንቅለ መንግሥቱ ሴራ ውስጥ ከተሳተፉ የጦሩ አባላት መካከል አንዳንዶቹ መፈንቅለ መንግሥቱ እንደሚሳካ ቀድመው እርግጠኛ በመሆን «እዚህ አድማ ውስጥ እኔንም አካፍሉኝ እንጂ ጎበዝ! በ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ሳይነግሩኝ ቀሩ። ዛሬም ልትተውኝ ነው እንዴ? ...» ብለው የተናገሩ የጦር መሪዎች እንዳሉ ስለመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው የተፃፉ ታሪኮች ያሳያሉ።

የመፈንቅለ መንግሥቱ ሴራ ጠንሳሾች «ታማኝ ናቸው» ያሏቸውን የጦሩን አባላት ሰብስበው ሲነጋገሩ ንግግራቸው ጭቅጭቅ የበዛበት ነበር። የመንግሥቱ ኃይለማርያም አስተዳደር ተወግዶ በምትኩ በጀኔራል መኮንኖች የሚመራ አዲስ መንግሥት የማቋቋም እቅዳቸውን ተናገሩ። በብዙ ጉዳዮች ላይ መግባባትና መተማመን እያጡ በሄዱ ቁጥር ጊዜ እየመሸባቸው መሆኑን መገንዘብ አቃታቸው።

የደህንነት ሚኒስትሩ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደሥላሴ በሊቀ መንበሩ ሽኝት ላይ ሳይገኙ የቀሩ የጦር አዛዦች ሁኔታ ስላላማራቸው አዛዦቹን የሚከታተል ቡድን አደራጅተው ስለነበር እያንዳንዱን ድርጊት ይከታተሉ ነበር። ጉዳዩ የመፈንቅለ መንግሥት አድማ መሆኑን ሲያረጋግጡም ነገሩን የሊቀ መንበሩ ቀኝ እጅ ለነበሩት ለሻለቃ መንግሥቱ ገመቹና ለሌተናል ጀኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን አሳወቋቸው።

ኮሎኔል አዲስ ተድላ እና ኮሎኔል ደበላ ዲንሳ በሽምግልና ወደ መከላከያ ሚኒስቴር ቢላኩም የመፈንቅለ መንግሥቱ ሴራ ጠንሳሾች ግን «ያለቀለት ነገር ስለሆነ ሽምግልናና ድርድር አያስፈልግም» ብለው መነታረካቸውን ቀጠሉ። ለመንግሥት ታማኝ በነበረው ጦርም ተከበቡ። በሁኔታው ተስፋ የቆረጡት አንዳንድ የጦር አዛዦችም ራሳቸውን አጠፉ።

የመፈንቅለ መንግሥቱ ጠንሳሾችና መሪዎች በፈፀሙት የእቅድና የአፈፃፀም ስህተት ለአራት ዓመታት ያህል ታቅዶበት ሲውጠነጠን የነበረው መፈንቅለ መንግሥትም ሳይሳካ ቀረ።

ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው በኋላ በተወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያም በርካታና «በአፍሪካ ደረጃ ምርጥ ነበሩ» የተባሉ የጦር መሪዎቿን አጣች። ደርግም የደመ ነፍስ ጉዞውን ቀጠለ። ሊቀ መንበር ሌተናንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከግንቦት 1981 መፈንቅለ መንግስት ቢተርፉም ከግንቦት 1983ቱ ግን ሳይተርፉ ቀሩ።

## የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከአገር መውጣት

ሌላኛው የዚህ ሳምንት ክስተት ደግሞ ከዚሁ ከግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም ክስተት የቀጠለው የደርግ ጣጣ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ ከግንቦት ስምንቱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራው ቢያመልጡም፤ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከመጣባቸው አውሎ ነፋስ ግን ማምለጥ አልቻሉም። ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ወጡ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዲሪ) ፕሬዚደንትና የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ (ኢሰፓ) ሊቀመንበር የነበሩት ሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አገር ጥለው የሸሹት ከ31 ዓመታት በፊት ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሰራዊት አባላትን ይወክላሉ የተባሉና ከተራ ወታደር እስከ ሻለቃ ድረስ ማዕረግ ያላቸው 120 የጦሩ አባላት ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ተሰብስበው ያቋቋሙት «የጦር ኃይሎች፣ የክብር ዘበኛ፣ የፖሊስ ሰራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ» መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከዙፋናቸው አውረደው። ስያሜውንም «ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ» ብሎ በመለወጥ ስልጣን ይዞ ኅብረተሰባዊነት (Socialism)ን የፖለቲካ-ኢኮኖሚ መርሁ አድርጎ አገር መግዛት ጀመረ።

የመሰረተ ልማት አውታሮችን በተለይ ደግሞ ትምህርትን ለማስፋፋት ከተደረገው ጥረት ባሻገር የእርስ በእርስ ጦርነት፣ እስራትና ስርዓት አልበኝነት የአገዛዙ መለያዎች ሆኑ። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል



ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከአገር ለቀው የወጡት ልክ በትናንትናው እለት ግንቦት 13 ቀን ነበር፣

በተለይ ደግሞ ኤርትራ ውስጥ ያለው ጦር ሲሸነፍ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የሚወስዱት እርምጃ፣ የሊቀመንበሩ የአቋም ግትርነት (ጀግንነት እንጂ ዲፕሎማሲ አይችሉም እየተባሉ ይታማሉ) እንዲሁም ሌሎች ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ተደምረው የጦሩ መሪዎች በሊቀመንበሩ ላይ ጥርሳቸውን ነከሱ።

መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግም ሞክረውም ሳይሳካ ቀረ። የአገሪቱ ችግርም ከድጡ ወደ ማጡ ሆነ።

ከዚህ ሁሉ ችግር ለማምለጥ ከአገር መውጣትን ምርጫቸው ያደረጉት የአገሪቱ ፕሬዚደንት ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በኬንያ በኩል አድርገው አሁንም ድረስ መኖሪያቸው ወደ ሆነችው ዚምባብዌ ገቡ። ኮሎኔል መንግሥቱ ከሚመሩት መንግሥት ጋር ሲዋጉ ከነበሩት አማፂያን መካከል «ሻዕቢያ» ኤርትራን ገነጠለ፤ ሕወሓትና አጋሮቹ ደግሞ ግንባር ፈጥረው ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ።

ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ የኢትዮጵያ ሬዲዮ ከመንግስት ምክር ቤት የሚሰጥ መግለጫ እንዳለ እየደጋገመ ሲገልጽ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ «ጦርነቱ ያስከተለው ሁኔታ እንዲለወጥ በልዩ ልዩ ወገኖች በልዩ ልዩ መልክ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ሆኖም ችግሩ አልተቃለለም። ይልቁንም ወደ ባሰ ደረጃ እየተሸጋገረ ይገኛል። ስለዚህ ደም መፋሰስ እንዲቀርና ሰላምም እንዲሰፍን በልዩ ልዩ ወገኖች የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ከስልጣን መውረዳቸው እንደሚበጅ የታመነበት ስለሆነ ይህንኑ በማመዛዘን ፕሬዚደንት መንግስቱ ኃይለማርያም በዛሬው ዕለት ከስልጣን ወርደው ከኢትዮጵያ ውጪ ሄደዋል። ፕሬዚዳንቱ ከስልጣን በመውረድ አገር ለቀው በመሄዳቸው የሪፐብሊኩ ምክትል ፕሬዚዳንት ሌተናል ጀኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ተክተው ይሰራሉ» የሚል አጭር መግለጫ ተላለፈ። በዚያው ኢህአዴግ አገሪቱን ተቆጣጠረ። የዚህን ዝርዝር በግንቦት 20 ታሪኮች እናየዋለን።

ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ግንቦት 13 ቀን ከአገር ከመውጣታቸው ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት የነበሩትን ሁነቶች ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ «አብዮቱና ትዝታዬ» በሚለው መጽሐፋቸው ያስታውሱናል።

ግንቦት 10 ቀን 1983 ዓ.ም ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም በመኖሪያ ቤታቸው ለከፍተኛ ባለስልጣኖቻቸው የእራት ግብዣ አደረጉ። ግብዣው ሲጠናቀቅ ፕሬዚዳንቱ ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ሁሉንም ተጋባዥ እንግዶች እበራፋቸው ላይ በመሆን አንድ በአንድ እየጨበጡ ሸኟቸው።

ግንቦት 12 ቀን 1983 ዓ.ም፤ ፕሬዚዳንት መንግስቱ መሉውን ቀን የተለያዩ ወረቀቶችን ቢሯቸው ውስጥ ሲቀዳድዱ ዋሉ፤ አመሻሽ ላይ ግን ወደ ዘመቻ መምሪያ በማቅናት ለከፍተኛ የጦር አዛዦቻቸው ንግግር አደረጉ።

ማክሰኛ ግንቦት 13 የፕሬዚዳንቱ ልዩ ረዳት ሻምበል መንግስቱ፤ ብላቴ ማሰልጠኛ ጣቢያ ደርሶ ከዚያም ወደ አስመራ ደርሶ መልስ የሚበቃ ነዳጅ የሞላ አንድ ዳሽ 5 አውሮፕላን እንዲዘጋጅ ትእዛዝ አስተላለፈ።

በዚያው ዕለት ከጠዋቱ ወደ 2 ሰዓት ገደማ ፕሬዚዳንቱ ከተመረጡ አጃቢዎቻቸው እንዲሁም ከሶስተኛ ክፍለጦር የመጣና የቅርብ አጃቢያቸው ከነበረው ከሻንበል ደመቀ ባንጃው ጋር በመሆን በኮሎኔል ተስፋዬ መሪነት ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በመድረስ ተዘጋጅታ ትጠብቅ ከነበረችው አውሮፓላን ተሳፈሩ።

ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ፕሬዚዳንት መንግስቱ የ 17 ዓመት ስልጣናቸውን ለቀው ከኢትዮጵያ ወጡ፤ እነሆ እስከ አሁን ድረስም በዚምባቡዌ ሐረሬ ይኖራሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# የማይነጥፈው ብእረኛ

አቤል ገብረኪዳን



የተወለደው በ1925 ዓ.ም ነው። ቦታውም በታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ነው። አባቱ መሪ ጌታ ዘሪሁን መርሻ የሚባሉ ሲሆን እናቱ ደግሞ ወይዘሮ አልጣሽ አድገህ ይባላሉ። አባቱ መሪ ጌታ ዘሪሁን የቤተ-ክህነት ሰው ስለነበሩ እና በዘመናቸውም የተማሩ ስለሆኑ ለልጃቸው ትምህርት የሚጨነቁ ነበሩ። እናም አራት ዓመት ሲሆነው እቤት ውስጥ ከርሳቸው ዘንድ የሚማረው ትምህርት ተጨምሮ የቤተ-ክህነትን ትምህርት ተማረ። የቤተ-ክህነት ትምህርት ከተከታተለ በኋላ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገባ። ይህ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ት/ቤት በመባል ይጠራ ነበር።

ገና በተማሪነቱ የማንበብ ልማድን ያዳበረው ብርሀኑ በተለይ የኢትዮጵያን ታሪክ በሚገባ መርምሯል ማለት ይቻላል። የብርሃኑ ዘሪሁንን ቀልብ ከሳቡት ታላላቅ መፃህፍት ውስጥ ደብተራ ዘነብ የፃፏቸው ታሪኮች ናቸው። አንደኛው የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክን የሚያወጣው መፅሀፍ ነው። ደብተራ ዘነብ በቴዎድሮስ ቤተ-መንግስት ውስጥ የነበሩ እና ከቴዎድሮስ ጎን የማይጠፉ የዚያን ዘመን ሊቅ ብሎም ፈላስፋ ናቸው። ታዲያ እርሳቸው የፃፉትን የአፄ ቴዎድሮስን ታሪክ ብርሃኑ ዘሪሁን ይወደው ነበር። ከዚህ መፅሀፍ በተጨማሪም ደብተራ ዘነብ "መፅሀፈ ጨዋታ ስጋዊ ወመንፈሳዊ" የተሰኘች መፅሐፍ አለቻቸው። ይህች መፅሃፍ ሃይማኖት ላይ መሰረት አድርጋ የተዘጋጀች ከኢትዮጵያ የፍልስፍና ጽሁፎች መካከል አንዷ ናት። ብርሃኑ ዘሪሁን ይህችን መፅሀፍ የመፅሀፎች ሁሉ ቁንጮ አድርጓት በየጊዜው ያነባት ነበር። የእነ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፤ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ እና የክብር ዶክተር ከበደ ሚካኤልም በብርሀኑ የንባብ ህይወት ውስጥ ከፍ ያለ ድርሻ አላቸው።

ብርሃኑ ዘሪሁን በ1945 ዓ.ም ላይ ብዙ እውቀቶችን ከገበየበት ጎንደር ከተማ ተነስቶ አዲስ አበባ መጣ። በአዲስ አበባም ቆይታው ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ገብቶ የሬዲዮ ቴክኒሻንነት በመማር በ1948 ዓ.ም ላይ በዲፕሎማ ተመረቀ። ታዲያ በዚያ በምረቃ ወቅት ከተማሪዎቹ ሁሉ አንደኛ ወጥቶ ተሸላሚ የነበረው ብርሃኑ ዘሪሁን ነው።

ብርሃኑ ዘሪሁን ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ሲማር የታላላቅ የአለማችንን ደራሲያን ስራዎችን ለማንበብ ዕድሉን አገኘ፡ የነ ዊሊያም ሼክስፒርን፣ የአሌክሳንደር ዱማስ ፔሬን፣ የቻርልስ ዲክነስን፣ የነ አሌክሳንደር ፑሽኪንን እና የሌሎችንም መፃህፍት አነበበ። እውቀቱንም እያስፋፋ መጣ። በንባብ የተከማቸው እውቀቱም በፅሁፍ መውጣት ጀመረ። እዚያው ተግባር-ዕድ ት/ቤ ሲማር የት/ቤቱ ልሳን የነበረችውን "ቴክኒ-ኤኮ" የምትሰኘውን መፅሄት አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪም እዚያው ተማሪ ሳለ በ1947 ዓ.ም ተውኔት ጽፎም አሳይቷል። እናም እንግዲህ በኢትዮጵያ ሥነ-ፅሁፍ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ሊወስድ ብርሃኑ ዘሪሁን የሚባል ብዕረኛ ወደ አደባባይ ብቅ ማለት ጀመረ።

ብርሃኑ ዘሪሁን ተግባረ ዕድ ውስጥ ውጤቱ ከፍተኛ ስለነበር እዚያው ት/ቤት ውስጥ ተቀጠረ። ከት/ቤቱ ውስጥም ሆኖ ለተለያዩ ጋዜጦች ይፅፍ ነበር። ከተግባረ ዕድ ት/ቤት በመልቀቅ በወቅቱ አጠራር የጦር ሚኒስቴር በአሁኑ መከላከያ ሚኒስቴር በሚባለው መስሪያ ቤት በአስተርጓሚነት ተቀጥሮ መስራት ጀመረ። እዚያም ብዙ ሳይሰራ 1952 ዓ.ም ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተዘዋወረ።

ብርሃኑ ዘሪሁን ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ወዲያው "የኢትዮጵያ ድምጽ" ተብሎ በሚታወቀው ጋዜጣ ላይ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሰራ። ታዲያ በዚህ ወቅት ጋዜጣዋን ታዋቂ ከማድረጉም በላይ በብዙዎች ዘንድ የሚነበቡ መጣጥፎችን እና ታሪኮችን በመፃፍ ዝነኛ እየሆነ መጣ። ቀጥሎም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ተዘዋወረ። ብርሃኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያዊያን አንባቢያን ልብ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ። በአንድ ጊዜ ስሙ እና ዝናው እየናኘ መጣ።

ብርሃኑ ዘሪሁን በድርሰት ዓለም ውስጥ በተለይ በ1958 ዓ.ም አዲስ የታሪክ አብዮት ማቀጣጠል ጀመረ። "የቴዎድሮስ ዕንባ" የሚሰኝ መፅሐፍ አሳተመ። መፅሀፉ የአፄ ቴዎድሮስን አነሳስ እና ለኢትዮጵያ ያላቸውን ርዕይ ብሎም የመጨረሻውን የህይወት ፍፃሜ የሚያሳይ ነበር። በወቅቱ ማለትም ብርሃኑ ይህን መፅሀፍ ከማዘጋጀቱ በፊት የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በጭካኔያቸው ላይ ተመስርቶ ብቻ የሚዘጋጅ በመሆኑ የቴዎድሮስን ውስጣዊ ስብዕና ያን ያህል ጎልቶ አይነገርም ነበር። እናም ብርሃኑ ዘሪሁን አፄ ቴዎድሮስ ብሔራዊ ጀግና መሆናቸውን የሚገልፅ ድርሰት ፅፎ በማቅረቡ በዘመኑ በጣም ታዋቂ ሆነ። ይህን "የቴዎድሮስ ዕንባ" የተሰኘውን ታሪክ መስፍን አለማየሁ ወደ መድረክ ቀይሮት በኢትዮጵያ የቴአትር አለም ውስጥም ከታላላቅ ቴአትሮቹ ተርታ የሚሰለፍ አድርጎታል።

ከዚያ በኋላ በተከታታይ በርካታ መጻህፍትን የጻፈ ሲሆን ከእነዚህም መሀከል .የእንባ ደብዳቤዎች፤ ድል ከሞት በኋላ፤ አማኑኤል ደርሶ መልስ፤ የበደል ፍጻሜ፤ ጨረቃ ስትወጣ፤ ብር አምባር ሰበረልዎ ተጠቃሽ ናቸው። የብርሀኑ ታሪክ ሲነሳ ግን ከፍተኛ ተጠቃሽ የሆኑት ሁለት መጻህፍት ናቸው። አንደኛው የታንጉት ምስጢር የተሰኘው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ ሶስት ጊዜ የተጻፈው .ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፤ ማዕበል የአብዮት መባቻ እና ማዕበል የአብዮት ማግስት የተሰኙት መጻህፍት ናቸው። እነዚህ መጻህፍት ብርሀኑ በኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ቦታ እንዲይዝ አድርገውታል።

ብርሃኑ ዘሪሁን ከደራሲነቱ ባሻገር ፀሐፊ-ተውኔት ነው። የቴአትር ፅሁፎችን በማዘጋጀት እና በኢትዮጵያ መድረክ ላይ ግዙፍ ሰብዕና የሰጡትን ስራዎች አቅርቧል። ከቴዎድሮስ እንባ በኋላ በ1972 ዓ.ም "ሞረሽ" የተሰኘ ተውኔት በብሔራዊ ቴአትር ቤት አቅርቧል። በ1975 ዓ.ም ደግሞ "ጣጠኛው ተዋናይ" የተሰኘ ተውኔት በሐገር ፍቅር ቴአትር ቤት አቅርቧል። በ1976 ደግሞ "የለውጥ አርበኞች" የተሰኘ ተውኔት ጽፏል። በኢትዮጵያ የታሪክ ተውኔቶች አለም ውስጥ በዘመን አይሽሬነታቸው ከሚጠቀሱት ቴአትሮች መካከል "ባልቻ አባነፍሶ" የተሰኘው ቴአትር ነው። ይህን ቴአትር በ1977 ዓ.ም የፃፈው ይኸው ጉምቱ ደራሲ ብርሃኑ ዘሪሁን ነው።

ብርሃኑ ዘሪሁን ከደራሲነቱ እና ከፀሐፊ ቴውኔትነቱ ባሻገር ሃያሲም ነበር። የተለያዩ ደራሲያንን ስራዎችን ፅሁፎችን እየተከታተለ ሂሳዊ መጣጥፎችን ያቀርብ ነበር። ከዚህ በላይ ደግሞ የተዋጣለት ጋዜጠኛ ሆኖ በዘመኑ በብዕሩ የናኘ ስብዕና የተጎናፀፈ ሰው ነበር።

ብርሃኑ ዘሪሁን እና "ድል ከሞት በኋላ" በሚል ርእስ ሂስ የጻፉት አቶ ባዩልኝ አያሌው ስለ ብርሀኑ የሚከተለውን ብለዋል በጽሁፋቸው ውስጥ።"የብርሃኑን ድርሰቶች በጥሞና ለመረመረ አንባቢ አንድ ነገር አይሸሸገውም። ይኸውም ደራሲው ከጊዜ ጊዜ እያደገና እየበሰለ መሄዱ ነው። ደራሲው በገፀ ባህርያት አሳሳል፣ በግጭት አፈጣጠር እና በአተራረክ ጥበብ እንዲሁም በአጻጻፍ ብልሀቱ እየሰላ ሲሄድ በድርሰቶቹ በጉልህ ይስተዋላል። ምንም እንኳን ሲመሰከር ባይሰማም ብርሃኑ አጭር፣ ቀጥተኛና ግልጽ አረፍተ ነገሮችን በድርሰቶች ውስጥ በመጠቀም፣ እንዲሁም ቀድሞ የነበረውን ተረታዊ የታሪክ መንገሪያ ስልት በመቀየር ፈር ቀዳጅ ከሆኑ የአገራችን ደራሲያን አንዱ ነው። ድርሰቶቹን የሚጽፈው እጅግ ቀላል እና ግልጽ በሆነ ስልት ነው። ከይዘት አንጻር አብዛኞቹ ድርሰቶቹም የሚያተኩሩት ማህበራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ነው።

የብርሃኑ ድርሰቶች ከቅርጽም ሆነ ከይዘት አንጻር ብዙ ሊባልላቸው የሚችሉ ናቸው። ሁሉም ድርሰቶቹ ማለት ይቻላል እጅጉን ለመነበብ የማይጎረብጡ ናቸው። ታሪክ ሲተርክም ሆነ መዋቅር ሲያበጅ ያውቅበታል። በየድርሰቶቹ የምናገኛቸው ገጸ ባህሪያቱ የቅርብ ሰዎችን ያህል የሚሰሙን ናቸው። የዚህም ምክንያቱ ምናልባት ማንነታቸው ከእኛ እንደ አንዱ ስለሆነ ታሪካቸውም እኛው የምንኖረው ያልራቀን፣ ያልረቀቀን አይነት ስለሆነ ይሆናል። በመሆኑም ስሜታቸውን ሁሉ እንድንጋራ እንሆናለን። የብዙዎቹ ድርሰቶቹ ጭብጦችም እንዲሁ ኑሮአችንና የየእለት ጉዳያችን ናቸው።

> **የብርሃኑ ድርሰቶች ከቅርጽም ሆነ ከይዘት አንጻር ብዙ ሊባልላቸው የሚችሉ ናቸው። ሁሉም ድርሰቶቹ ማለት ይቻላል እጅጉን ለመነበብ የማይጎረብጡ ናቸው**

ብርሃኑንና ድርሰቶቹን ሳስብ ሁሌም የሚደንቀኝ አንድ እውነት አለ። ያለኝ መረጃ እርግጥ ከሆነ ብርሃኑ ለብዙ ዓመታት ጋዜጠኛ፣ በኋላም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር። የጋዜጣ ስራ ደግሞ ምን ያህል ጊዜን እንደሚወስድ ብቻ ሳይሆን አድካሚና የአፍታ ረፍት የለሽ መታተር እንደሆነ እናውቃለን። ዛሬ ለነገ ሰርቶ ዛሬውኑ ለቀጣዩ ቀን ማሰብን፣ መሮጥን ያለ ረፍት መድከምን... ይጠይቃል። ጋዜጣው እለታዊ ሲሆን ደግሞ አስቡት። የጋዜጣው አዘጋጅ ሲኮንስ? ሌላ ሌላውን ትተን ዋና አዘጋጁ ቢያንስ በየእለቱ ርዕሰ አንቀጽ መጻፍ ይጠበቅበታል። እንግዲህ በዚህ ሁሉ ውጥረት ውስጥ ሆኖ ነው ብርሃኑ በቁጥር የበዙ በጥራትም የላቁ ድርሰቶችን የጻፈው። ይህ ሁሌም ያስገርመኛል።"በማለት ብርሀኑን አሞግሶታል። አገርን እና ትውልድን በብዕሩ ቀለማት ሲዘክር የኖረው ይህ ሰው ሚያዚያ 16 ቀን 1979 ዓ.ም በ54 ዓመቱ ከዚህ አለም በሞት ተለየ። ቀብሩም በባለወልድ ቤተ-ክርስቲያን ተፈጽሟል።




# ባስተሰጥዖው የሰሜን ወሎ ታዳጊ



እፀገነት አክሊሉ

ልጆች እንደምን ከርማችኋል ደህና ናችሁ ወቅቱ የሙከራ ፈተናዎች እየተሰጡበት ያለ ከመሆኑ አንጻር ፈተና እንዴት ነበር፤ እርግጠኛ ነኝ በጥሩ ሁኔታ ፈተናውን ሰርታችኋል። ደከም ያላችሁበት የትምህርት ዓይነት ካለ ደግሞ ለቀጣዩ በደንብ በማጥናት ጥሩ ውጤት ለማምጣት ስሩ እሺ።

ልጆች ዛሬ ማህበራዊ ድረ ገጽ ላይ ሳነብ ካገኘሁት ላይ አንድ በሰሜን ወሎ ክልል ያለ ባለተሰጥዖና ጎበዝ ተማሪ የሆነ ታዳጊ ልጅ አስተዋውቃችኋለሁ።

ስሙ ህጻን ሳሙኤል ዳርጌ ይባላል። ተወልዶ ያደገው በሰሜን ወሎ ዞን ራያና ቆቦ ወረዳ በሮቢት ከተማ ነው። እድሜው 12 ዓመት ሲሆን በአሁኑ ወቅት የ9ነኛ ክፍል ተማሪ ነው። ይህ ደግሞ በጣም አስገራሚ ነው። ልጆች ህጻን ሳሙኤል ትምህርት የጀመረው በ4 ዓመቱ ሲሆን የትምህርት አቀባበሉ በጣም ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ በ7 ዓመቱ ስድስተኛ ክፍልን ሊያጠናቅቀ ችሏል። ይህ እንግዲህ በአንድ አመት ሁለት የክፍል ደረጃዎችን አጠናቋል እንደማለት ነው ።

ከስድስተኛ ክፍል በኋላ ግን የትምህርት ቤቱ መመህራን ልጁ በጣም ህፃን ከመሆኑ የተነሳ በክፍሉ ካሉ ተማሪዎች ጋር በአካል መመጣጠን እንደማይችል ከዚህ በኋላ በአመት አንድ ክፍል ብቻ መማር እንዳለበት ወሰኑ። ልጆች መምህራኑ ይህንን ውሳኔ ባያሳልፉ ኖሮ ህፃን ሳሙኤል በ12 ዓመቱ 11ኛ ክፍል ላይ ነበር የምናገኘው።

ልጆች ህጻን ሳሙኤል 7 እና 8ተኛ ክፍልን ሲማር ከመላው ክፍል (ሴክሽን) አንደኛ በመውጣት ነበር ያጠናቀቀው። ህጻን ሳሙኤል ትምህርትን አብዝቶ የሚወድ ብዙ ጊዜውንም በጥናት የሚያሳልፍ ቢሆንም ከትምህርት ጊዜና ከጥናት ውጪ ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን ለእናትና ለአባቱ ያደርጋል። ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከልም እናትና አባቱ የመንግስት ሰራተኞች በመሆናቸው ለስራ ውጤታማነት የሚያግዟቸውን እቅዶች ያወጣላቸዋል። በእቅዶቹ ላይ ማብራሪያ ይሰጣቸዋል እንዴት አድርገው ቢሰሩም ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ያማክራቸዋል። በዚህም በስራ አፈጻጸማቸው በጣም ውጤታማ ናቸው ይላል ስለ ህጻን ሳሙኤል በማህበራዊ ሚዲያው የተገለጸው መረጃ።

ህጻን ሳሙኤል ከትምህርት ውጪ ያሉ መጻህፍትንም በማንበብ በኩል ጥሩ ልምድ አለው ለምሳሌ በዶክተር ሮዳስ ታደሰ የተዘጋጀውን አንድሮሜዳ መጽሃፍ ለማንበብ የፈጀበት ሁለት ቀናት ብቻ ነው። ህጻን ሳሙኤል አድጎ መሆን የሚፈልገውም የስነ -ፈለግ ተመራማሪ ነው። ምኞቱ እንዲሳካለትም እንመኛለን።

ልጆች እናንተም በትምህርታችህ ውጤታማ እንድትሆኑ ጊዜያችሁን በአግባቡ ተጠቀሙ ፊልምና ሌሎች መዝናናቶችን ቀንሳችሁ ማንበብ ላይ ትኩረታችሁን አድርጉ።

# ስፖርት





## የእግር ኳስ ደጋፊዎች ሲከበሩ!

ቦጋለ አበበ

በተወዳጁ የአለማችን ስፖርት እግር ኳስ ደጋፊዎች ከምንም በላይ ትልቅ ቦታ አላቸው። ደጋፊዎች የእግር ኳስ ውበትና የካምቦሎጆ ድምቀት ብቻ አይደሉም። የአንድ ክለብ ወይም ብሔራዊ ቡድን የጽናት፣ የአሸናፊነትና የስኬታማነት ሚስጥር ጭምር ናቸው።

ደጋፊዎች በሁሉም የአለማችን ክለቦችና ብሔራዊ ቡድኖች እንቅስቃሴ በገንዘብ፣ በማህበራዊና በስሜታዊነት የቆሙ በመሆናቸው በየትኛውም የዓለም ማእዘን ውስጥ ባሉ በማንኛውም የስፖርት ቡድን ውስጥ ቁልፍ ተጫዋች ተደርገው ይቆጠራሉ።

ደጋፊዎች በማንኛውም ግጥሚያ ላይ የቡድናቸውን ተጫዋቾች ካላሰፈላጊ ጫና ሲከላከሉ፣ ሲያጀግኑ፣ በተፎካካሪዎቻቸው ላይ ሲጮሁ፣ አሸናፊዎቹንና አስተዳዳሪዎቻቸውን በማምለክና ከቡድናቸው ብሔራዊ መዝሙር ጋር በማመሳሰል አስደናቂ የሙዚቃ ቅኝት ሲያሰሙ ቡድናቸው ራሱ በተቃዋሚዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጥር እንደሚችል ማንም ያውቃል።

ታማኝ ደጋፊዎች በማንኛውም ጨዋታ ስታዲየሞች ዋና ንጥረ ነገሮች በመሆናቸው የሚወዱት ክለብ እየተሸነፈም ማበረታታት በጭራሽ አያቆሙም። ቡድናቸው የቱንም ያህል ወደ ውጤት አዘቅጥ ውስጥ እየገባ ውብ ዝማሬ አይነጥፍባቸውም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወደ 250 ሚሊዮን የሚጠጉ የተለያዩ የእግር ኳስ ቡድኖች ወይም ክለቦች የታወቁ አድናቂዎች ወይም ደጋፊዎች በዓለም ዙሪያ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ቀንደኛ የእግር ኳስ ደጋፊዎች በየትኛውም አለም ሊገኙ ይችላሉ። ከነዚህ መካከል ጥቂቶች ቡድናቸው



አይነ ስውሩ ደጋፊ በሕይወት ባይኖርም በሜስታላ የዘላለም ሐውልት ቆሞለት ይገኛል፣

በየትኛውም አይነት ውጣ ውረድና ቀውስ ውስጥ ቢገባም ዘወትር ካምቦሎጆ ተገኝተው ከመደገፍ በዘለለ ርቀት ሳይገድባቸው ሌሎች ጉዳዮቻቸውን ወደ ጎን በመተው ለቡድናቸው የትኛውንም መስዋዕትነት የሚከፍሉ ጥቂት አይደሉም። እንደነዚህ አይነት ደጋፊዎች በኢትዮጵያ እግር ኳስም ውስጥ ይገኛሉ። ከአርባ አመታት በላይ የቀድሞውን መብራት ሃይል የአሁኑን ኢትዮ ኤሌክትሪክ በመደገፍ በልዩነት የሚጠቀሱት በቀለ ሄኒ (ኮረንቲ) ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው። እኚህ አንጋፋ ደጋፊ በቅርቡ ህይወታቸው እስካለፈበት እለት ድረስ ቡድናቸውን ከአራት አስርት አመታት በላይ በየትኛውም ሁኔታ በታማኝነት ከመደገፍ አልፈው በአንድ ወቅት የቡድናቸው ወሳኝ ተጫዋቾች ወደ ሌላ ክለብ እንዳይዘዋወር እቤታቸውን እስከ መሸጥ ውሳኔ ላይ የደረሱ ታማኝ ደጋፊ ሆነው በሌሎች ክለብ ደጋፊዎችም ይሁን በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ሁሌም በክብር ይታወሳሉ።

የዛሬው ስፖርት ማህደር አምዳችንም ወደ ስፔን አቅንቶ በአለም ዙሪያ በተለየ ሁኔታ የሚታወስ አስደናቂ የእግር ኳስ ደጋፊን ታሪክ ያወሳል። ይህ የተለየ ደጋፊ ማን እንደሆነ የስፖርቱ ቤተሰብ ከመንደርደሪያው በቀላሉ ሊገምት ይችላል። ቪሴንቴ ናቫራ አፓሪቺዮ - አይነ ስውሩ ደጋፊ! በአለም ዙሪያ ገናና ስም ያለው እግር ኳስ አፍቃሪ ነው።

አፓሪቺዮ የስፔኑን ክለብ ቫሌንሲያ የውጤት ከፍታና ዝቅታን የተመለከተ፣ በክፉውም በደጉም ዘመን ከክለቡ ጋር ሁሉንም ስሜቶች የተጋራ አንጋፋ ደጋፊ ነው። እግሮቹም ለዘመናት ወደ ሜስታላ ለማቅናት አልደከሙም።

በስታድየሙ ፊትለፊት “ትሪቡና ሴንትራል” በሚባለው በ 15ኛው ረድፍ በቁጥር 164 መቀመጫ ላይ የአመት ትኬት ስለሚገዛ የስፖርቱ ቤተሰብ በዚያ ቦታ ላይ ከአፓሪቺዮ ውጪ የተቀመጠ ደጋፊን ማስታወስ አይቻለውም።

ይህ ክለቡን በታማኝነት ከልቡ በመነጨ ስሜት ሲደግፍ የኖረ ሰው ከአርባ አመታት በፊት በህይወቱ ነገሮች መልካቸውን ቀየሩበት። አንጋፋው ደጋፊ የሚወደውን ክለብ በአይኑ እየተመለከተ እንዳይዝናና አይኑ ላይ የጤና እክል ገጠመው።

አፓሪቺዮ በአይኑ የኋላ ክፍል የምትገኝ ስስ አካሉ ነገር (Retina) ላይ ችግር መኖሩን ያወቀው አይኑ ከተጎዳ በኋላ ነበር። ህክምናው በመዘግየቱም የአይን ብርሀኑን መልሶ ለማግኘት ሳይታደል ቀረ። የሜስታላን ደጋፊን የስቴድየም ድባብ በአይኑ እየተመለከተ፣ በአፍንጫው እያሸተተና በእጁ እየዳሰሰ ልባዊ ድጋፉን ለክለቡ ሲቸር የነበረው መልካም ዘመን ግን አይኑ ቡድኑ ሲጫወት ማየት ባለመቻሉ ታሪክ ሆኖ አልቀረም።

ይህ ደጋፊ አይነስውር ሆኖም ለዘመናት ልባዊ ድጋፉን ሲሰጠው ከኖረው ክለቡ አላራራቀውም። የአይኑ ጨዋታዎችን አለማየት ከካምቦሎጆ ደጅ አላስቀረውም። የአመት የስቴድየም መግቢያ ትኬት እየቆረጠና ቦታው ላይ እየተቀመጠ በሜስታላ መታደሙን ቀጠለ። አይኑ ባያይም በሌሎች የስሜት ህዋሳቶቹ የስታድየሙን ድባብ በመካፈሉ ገፋበት።

አፓሪቾ እኤአ 2017 ላይ ባጋጠመው ህመም የሚወደውን ክለብ ትቶ ወደማይቀረው ሞት አመራ። ብዙዎቹ ደጋፊዎች ግን የሱን መቀመጫ ካለሱ ሲመለከቱ እንባቸው ይቀድማቸው ነበር። አንጋፋው ደጋፊ አጠገባቸው ባይኖርም እንኳን ፅናቱን ግን ተምረውበታል። ክለቡ ቫሌንሲያም ቢሆን የዚህን አስደናቂ ደጋፊ ታሪክ እንደ ቀላል አልተመለከተውም። ፅናቱን የሚያወድስ እንዲሁም የደጋፊዎችን ስሜት የሚመልስ ድንቅ ስራ ሰርቷል። ሁሌም የሚታወስበትን አስደናቂ ታሪክም መቼም እንዳይረሳ አድርጎ ለመጪው ትውልድ አኑሮለታል።

ቫሌንሲያ ክለብ የአንጋፋውን ደጋፊ ቪሴንቴ ናቫራ አፓሪቺዮ ሀውልት አሰርቶ እርሱ በሚታወቅበት በ”ትሪቡና ሴንትራል” በሚባለው በ 15ኛው ረድፍ በቁጥር 164 መቀመጫው ላይ አስቀምጦ የዘለአለም የክለቡ ጨዋታ ላይ እንዲታደም አድርጎታል።